# ማ ዕ ዶ ት



ጌታችን በዮርዳኖስ ሲጠመቅ

ቍጥር ፲፫

ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማዕዶት

ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ. ም.

አዲስ አበባ

ቍጥር ፲፫

www.ethiopianorthodox.org

« ማ ዕ ዶ ት »

ማዕዶት የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ ከልሳነ ግዕዝ ሲሆን ትርጓሜውም መሸጋገሪያ ማለት ነው ። ይህ መጽሔት በዚህ በሽግግር ወቅት በተሐድሶ ላይ የምትገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያንን እምነትዋንና ሥርዓቷን ባሕሏንና ወቅታዊ እንቅስቃሴዋን ዜናዋንና ታሪኳን ልዕልናዋን ሁሉ የሚገልጽ ስለሆነ «ማዕዶት» ተብሎ ተሰይሞአል ።

ይህ መጽሔት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽሕፈት ቤት በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር አንድ ጊዜ ታትሞ ይወጣል ።


ዋና አዘጋጅ ፡

ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም
ስልክ ቁጥር 110754
ፖ - ሣ - ቁጥር 1283


ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም
አዲስ አበባ

ማ ው ጫ


| ተራ ቊ | አ ር እ ስ ት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ | ፭ |
| ፪ | የቅዱስነታቸው ቃለ ምዕዳን | ፮ |
| ፫ | የቅዱስነታቸው የሥራ ጉብኝት | ፯ |
| ፬ | ቅዱስነታቸው ለ፲፩ ወጣቶች የምስክር ወረቀት ሰጡ | ፰—፲ |
| ፭ | የጠ/ሥራ አስኪያጁ የሥራ ጉብኝት | ፲—፲፯ |
| ፮ | የአጠቃላይ ሰበካ መ/አስተዳደር ጉባኤ | ፲፯—፲፱ |
| ፯ | ለልዑካኑ የሁለት ቀን ሰሚናር ተሰጠ | ፲፱—፳፩ |
| ፰ | የጫጋል መ/ዓለም ቅዳሴ ቤት ተከበረ | ፳፩—፳፫ |
| ፱ | በዓታ ለማርያም | ፳፫—፳፬ |
| ፲ | ሳሙኤል ዘዋልድባ | ፳፭—፳፮ |
| ፲፩ | ዘመነ ስብከት | ፳፮—፳፯ |
| ፲፪ | ተአምራታዊ ዜና | ፳፰—፳፱ |
| ፲፫ | የመጀመሪያው ተአምር | ፴ |
| ፲፬ | ሰላም በምድር | ፴—፴፫ |
| ፲፭ | የምወደው ልጅ | ፴፬—፴፭ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

www.ethiopianorthodox.org

# «ርእሰ አንቀጽ»

«ለእግዚብሔር ክብር ይሁን ለሰውም በጎ ፈቃድ»

ዓለም በኃጢአት ጨለማ ተውጦ ሰውና እግዚአብሔርም ተለያይቶ ፣ ሰላም ከሰው ልጆች መካከል ጠፍቶ በምትኩ ጥል ፣ ክርክር ፣ ምንዝር ፣ ነፍስ መግደል አምልኮ ባዕድና ሌላው ኃጢአት ሁሉ በዓለም ላይ ተስፋፍቶ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሙሉ እንደ ኖረ ታሪክ ይነግረናል ።

ነገር ግን ሰላም ፣ ፍቅር ፣ ፍትሕና ፣ ርትዕ የሚገኘው ከማን በማን እንደሆነ ነቢያት በየጊዜው እየተነሡ ይተነብዩ እንደ ነበር ከብሉይ ኪዳንና ከነቢያት መጻሕፍት አንበን እንረዳለን ። ይኸውም ሰላም ፣ ፍቅር ፣ ትሕ ትና ፣ ርኅራኄ ፍትሕና ርትዕ የሚገኘው ሁሉን ከሚችል ከእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን በግልጽ ያስረዳል ።
ሰላም በምድር ለሰው ልጆችም በጎ ፈቃድ እንዲሆን እግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ላከልን ። እርሱም ነቢዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ «ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ሲል መስክሮለታል ። ስለሆነም ክርስቶስ በቤተ ልሔም በላሞች ግርግም ሲወለድ መላእክት ከሰ ማይ ወደ ምድር ከምድር ወደ ሰማይ እየተመላለሱ»ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ» እያሉ በዘመሩ ጊዜ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ እንደፈረሰ በምትኩም ሰላም ፣ እርቅና ምህረት በምድር ላይ እንደ ሰፈነ የሐዲስ ኪዳን መጻ ሕፍት ያስረዱናል ።

ክርስቶስ በቤተ ልሔም በሚወለድበት ጊዜ በመላእክትና በኖሎት አንደበት (ልሳን) የሰላም አዋጅ እንደ ተነገረ ቅዱስ ወንጌሉ ጨምሮ ተርኮልናል ።
በዚሁ ዕለት ሰውና መላእክት ብቻ አመስግነው አልቀሩም ፣ እንስሳት ፣ አራዊት ፣ የሰማይ አዕዋፍና የባ ሕር ዓሣት ሳይቀሩ ሰላም በምድር ተመሠረተልን እያሉ ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል ። ምክንያቱም ሰላም በምድር ከሌለ ማንኛውንም ፍጡር በሰላም ለመኖር አይችልምና ነው ።
በተለይም በዚሁ በተቀደሰ ልደቱ የገለጸውን የቸርነት ምሥጢርና በዙሪያቸው ያበራውን ብርሃን በቅርብ ሁነው ለማየት የታደሉ ዮሴፍና ሰሎሜ ሲሆኑ በመላእክት ተጠርተው የደስታው ተካፋዮች የሆኑትም በቤተ ልሔም ዙሪያ መንጋቸውን ተግተው ይጠብቁ የነበሩት የከብት እረኞች ናቸው ።
ከዚያም በኋላ ይህን የሰላም ባለቤትና እውነተኛ ብርሃን ለማየት የታደሉ ሰ፡እሰገል የምሥራቅ ነገሥታት ለአምላክነቱ ለንጉሥነቱ የሚገባውን እጅ መንሻ ይዘው በኮከብ እየተመሩ ከቤተ ልሔም ደርሰው የልደቱ በዓል ተካፋዮች ሁነዋል ።

እንግዲህ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ የሰዎችን ፍቅር አገብሮት ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ከተወለደ በኋላ ለእናቱ እየታዘዘ አደገ በሰላሳ ዓመቱም በአገልጋዩ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ በዚሁም ወቅት እግዚአብሔር አብ በደመና ሆኖ «ይህ ነው የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት» ብሎ ሲናገር መንፈስ ቅዱስም በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲያርፍ ዮሐንስ አይቶ መስክሮአል ።

እነሆ አንድነቱንና ሦስትነቱን በጎላና በተረዳ ተገልጾአል በዚሁ ጊዜም ዲያብሎስ የአዳምና ሔዋን ስመ ግብርናት ጽፎ በዮርዳኖስ ወንዝ(ባሕር)ሸሽጎት የነበረውን ክርስቶስ በማዕከል ባሕሩ እንደቆመ እንደገል ተቀ ጥቀጦ እንደ ሰም ቀልጦ ጠፍቶአል ፣ ተደምስሶአል ። በዚሁ ጊዜ ተራሮች ዘለዋል ባሕርም ሸሽቶአል ልዩ ልዩ አስደናቂ ተአምራትም ታይቶአል ።

ክርስቶስ በልደቱና በጥምቀቱ የመሠረተልን ሰላምና ፍቅር እነሆ በዓለም የሚገኙት ክርስቲያኖች ሁሉ ስለ ልደቱና ስለ ጥምቀቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ሲያከብሩት ይኖራሉ ። በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና ጥምቀት ያላት አከብሮት ከሌሎቹ በጣም የተለየ ነው ። የዓለም ሰዎች በዓለ ጥምቀቱን ለማየት በቱሪስት መልክ ወደ ኢትዮጵያ በብዛት ይመጣሉ ። በዓለ ልደትና በዓለ ጥምቀት ልዩ ክብር ሊሰጠው የሚገባ ነው ።
በእርግጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደትና በዓለ ጥምቀት ልዩ ክብር ሊሰጠው የሚገባ ነው ። ምክንያቱም በልደቱ ከእግዚአብሔር ተወልደናል በጥምቀቱም ተጠምቀን ሁለተኛ ልደት አግኝተናል ከዲያብ ሎስ አገዛዝ ነፃ ወጥተናል ከጨለማ ወደ ብርሃን ተሸጋግረናል ከፍርሃት ከሽብር ከጥል ከክርክር ወጥተን ሰላምና ፍቅር አግኝተናል ።

ስለዚህ ይህ የጌታ ልደትና ጥምቀት ለማየት የታደሉ ዓይኖች ለመስማት የበቁ ጆሮዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ አክብረን ለመክበር እንድንበቃ በዓሉን በደስታና ከልብ በመነጨ ስሜት ተሞልተን ለእግዚአብሐር ክብር ይሁን ለሰውም በጎ ፈቃድ እያልን እምነታችንን መግለጽ አለብን ።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት ምክንያት በማድረግ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሬድዮና በቴሌብዥን ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ።

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

የኢትዮጵያን ምድር ዳር ድንበር ለማስከበር ኅብረተ ሰቡን ለመጠበቅ በየጠረፉና በመሐል ሀገር ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ፤ በገጠርና በከተማ የምትኖሩ ምእመናን ፤ በሕመም ምክንያት በሐኪም ቤቶች የምትገኙ ሕሙማን ሁላችሁ ፤ የዓለም ብርሃን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ለብርሃን ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ ። የሰው ዘር ሁሉ አባት የሆነው አዳም የፈጣሪውን ሕግ በመተላለፍ በፈጸመው የደል ምክንያት በፊት የነበረውን ክብርና ደስታ ሰላም አጣ ፤ በጭንቀት ላይ ወደቀ በአንድ በአዳም በደል ምክንያት ክፉ ሥራ በሰዎች መካከል ተስፋፋ አዳምም የፈጣሪውን ትእዛዝ ተላልፎ በሠራው በደል ተጸጽቶ አለቀሰ ንሥሐም ገባ ፈጣሪው እግዚአብሔርም ኃዘኑን ተመልክቶ ጸሎቱንና ልመናውን ሰምቶ አንድ ልጁ ንእግዚአብሔር ወልድን ልኮ ዓለሙን ሁሉ ያድነው ዘንድ ወደደ ። በራሱና በአብ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሰው ሆኖ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ እግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም በመምጣቱና ሰው በመሆኑ በአዳም በደል ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የሰዎችና የእግዚአብሔር ግንኙነት ታድሶ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል እርቅና ሰላም ሆነ ። ሰው ከፈጣሪው ጋር በመታረቁ በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ እጅግ ተደሰቱ ስለዚህም በሰማያት ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን በምድርም ለሰው ዘር ሰላምና በጎ ፈቃድ ተሰጠ በማለት ሰውና መላእክት በአንድነት ዘመሩ ። እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል ሲል በአዳም ኃጢአት ምክንያት በዓለም ላይ የነበረው ኃዘን ጭንቀትና ሞተ ነፍስ በክርስቶስ ልደት ተወግዶ የመንፈስ ሰላምና ደስታ የህሊና ዕረፍት ድኅነተ ነፍስ ተገኘ። (ሉቃስ ፪ ፡ ፲)።

የክርስቶስ ልደት በጨለማ ለነበሩ ብርሃንን በኃጢአት ለነበሩ ሥርየትን በግዞት ለነበሩ ነፃነትን አስገኝቶአል ይህንንም «በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃንን አየ ፤ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው ይላል (ኢሳ ፱ ፡ ፪ ማቴ ፫ ፡ ፲፫) ።

እግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም እንደሚመጣና ሰው ሆኖ ከድንግል እንደሚወለድ ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት ተናግሮ ነበር ትንቢቱም«ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል። አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ። ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም የሚል ነው ። (ኢሳይ ፱ ፡ ፮-፯) ።

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተገለጠው የእግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም መምጣትና ሰው ሆኖ በድንግልና መወለዱ የፈጠረውን የሰው ልጅ ሁሉ ምን ያህል እንደሚወደውና እንደሚያከብረው እንረዳለን ።

ይህንን የክርስቶስ የልደት በዓል በምናከብርበት ዕለት ልናስበው የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ አለ ። ይኸውም ነፃነታቸውን አጥተው በባዕድ ጽኑ አገዛዝ የተጨነቁ ነፃነትንና እኩልነትን እንዲያገኙ ፤ ከትምህርት ዓለም ርቀው በጨለማ ውስጥ ያሉ ትምህርትን እንዲያገኙና በዕውቀት እንዲጐለምሱ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ አጥተው የተቸገሩ ወገኖቻችን ከገጠማቸውና ከደረሰባቸው ችግር እንዲድኑ አሁንም ዓለምን በማስቀቅና በማስጋት ላይ የሚገኘው የጦር መሣርያ ብዛት ተቀንሶ ፍቅርና ሰላም እንዲሰፍን ጥፋት እንዲወገድ ነፃነትና እኩልነት ተከክለኛ ፍትሕና ርትዕ በኅብረተ ሰብእ መካከል እንዲኖር ማዘን መጸለይና ለደረግ የሚገባውን ሁሉ ማድረግ ነው

የሰላም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሀገራችንን ኢትዮጵያን በነፃነት ለዘለዓለም ይጠብቅልን ። ለዓለም ሁሉ ሰላምን ይስጥልን ።



# የቅዱስነታቸው የሥራ ጉብኝት ፤

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በቀጨኔ አካባቢ የሚገኘው የደራ ገዳም መጦሪያ ቅርንጫፍ ማኅበር ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፸፭ ዓ/ም ከሥፍራው ተገኝተው ጉብኝት አድርገዋል ።



ቅዱስ ፓትርያርኩ የማኅበረ በዐር እደ ጥበባት በጐበኙበት ወቅት

ቅዱስነታቸው እስፍራው እንደ ደረሱ የገዳሙ ኃላፊ ሊቀ ጠበብት ወልደ ማርያም ወንድምኩን እደራ ታላላቅ የሠፈሩ አዛውንትና ሕዝብ ከፍ ያለ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው በገዳሙ አስተዳዳሪ በሊቀ ጠበብት ወልደ ማርያም አማካይነት ልዩ ልዩ እደጥበባት ወደሚሠሩበት ክፍል በማምራት እየተዘዋወሩ ከጐበኙ በኋላ በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ተገኝተው አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋል ። ከዚህም አያይዘው አባታዊ ምክር አስተላልፈውላቸዋል ።

«በሥራችን መጠቀም እንደሚገባን የሃይማኖታችን መሠረት የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ያዘናል ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ያልሠራ አይብላ ሲል አዟል ፤ የምትሠሩት ሥራ ሁሉ ኅብረተሰቡን የሚያገለግል ስለሆነ የሚያኮራና የሚያስመሰግን ነው እንጂ የሚያስነቅፍ አይደለም ። እናንተም እንደዚህ ተብለናል ብላችሁ የሚያሳዝናችሁ ሳይሆን የምትደሰቱበትና የምትኮሩበት ተግባር ነውና በሥራችሁ መበርታት ይገባችኋል ። »

«በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሁሉ ወንድማማች ነው ፤ ስለሆነም አሁንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና»ካለ በኋላ«አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንዲያስ የአብርሃም ዘር እንደተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ» ብሎ እንደሚነግረንና እንደሚያስተምረን ሁሉ የምንከተለውና የምንፈጽመው የምናስፈጽመውም ይህ መልእክት ነው» ብለዋል ።

ከዚህ ቀደም ብሎ ግን ሊ/ጠበብት ወልደ ማርያም ወንድምኩን እደራ አጠር ያለ ንግግር አድርገዋል ። ከንግግራቸውም ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረንና እንደሚያስተምረን ከሆነ በዓለም ላይ የሚገኝ ሰው ሁሉ የአዳምና የሔዋን ዘር ነው ። ታድያ ይህ ከእነዚህ ሁለት ሰዎች የተገኘው ትውልድ የገዛ ወገኑና የገዛ መሰሉን ልዩ ልዩ ስም እየሰጠ መለያየትንና መጣላትን እየፈጠረ ሰላም በምድር እንዳይሰፍን የሰላም ጠንቅ በማየታችን በጣም እናዝናለን ።

በሀገራችንም ይህን የመሰለ አሳዛኝ ስም በመስጠት ወገኖቻቸውን የሚያርቁና ከወገኖቻቸውም የሚርቁ ብዙዎች ናቸው ። ይህም ከንቱ ሀሳብ አንዳንድ አሉባልተኞች በመከተል ነው ። አሁን ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ቅዱስነትዎ እኛን የጠፋን መንጎችዎ ለመፈለግ በመካከላችን በመገኘትዎ ለደስታችን ወሰን የለውም የሚል ደገኝበታል ።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ለገዳሙ የሚሆን ርዳታ ከልማትና ክርስቲያናዊ መምሪያ እንደሚላክላቸው አባታዊ የተስፋ ቃል ሰጥተዋቸዋል ። እንዲሁም ገዳሙን ማኅበረ በዐር የገዳሙ ኃላፊ መምህር ወልደ ማርያም ወንድምኩን እደራ ሊ/ጠበብት ብለው ሰይመዋቸዋል ። መርሐ ግብሩ በዚሁ እንደተጠናቀቀ ቅዱስነታቸውም ወደ መንበራቸው ተመልሰዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስነታቸው ለ፲፩ ወጣቶች የምስክር ወረቀት ሰጡ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትር ያርክ ዘኢትዮጵያ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት በልዩ ልዩ ጥባበተ እድ ለሰለጠኑ ፲፩ ወጣቶች ጥር ፫ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በስብከተ ወንጌል አዳራሽ የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል ።

ወጣቶቹ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በወሎ ክፍለ ሀገር በወረደው የረሀብ በረዶ ምክንያት አባት እናታቸው የሞቱባቸው ሲሆኑ በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ሕፃናቱን ሰብስባ የሕፃናት አስተዳደግም እቋቁማ በጥሩ እንክብካቤ ያሳደገ ቻቸው ናቸው ።

የምረቃው ስነ በዓል በትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤትና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን የሕ ፃናት አስተዳደግ ድርጅት የተዘጋጀ ሲሆን ለዕለቱ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ስነ ሥርዓቱ ተከ ናውኖአል ።

በመጀመሪያ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይ ማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ከቀኑ አራት ሰዓት ሲሆን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና የየመምሪያ ኃላ ፊዎችን አስከትለው በስብከተ ወንጌል አዳራሽ እንደ ተገኙ በወጣቶቹ የተዘጋጀ የአበባ ዕቅፍ በደ ናግሉ ተበርከቶላቸዋል ። ወዲያውኑ ቅዱስነታቸው በዓሉን በጸሎት ከፍተዋል ።

ከዚሁም በማያያዝ ዶክተር ደርቤ ወልደ ጻድቅ የማተሚያ ቤቱ ም/ሥራ አስኪያጅ መርሐ ግብሩን በመምራት ሊ/ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ የማ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ስለ በዓሉ አጭር መግለጫ እንዲ ሰጡ አሳስበዋል ።

ሊ/ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ ባደረጉት ንግግር «ከሁሉ አስቀድሞ በዛሬዋ ዕለት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመካከላችን ስለተ ገኙልን የተሰማንን ልባዊ ደስታ በታላቅ ትሕትና እገልጻለሁ» ካሉ በኋላ «በዚህች የመንበረ ፓትርያ ርክ ጽርሕ (አዳራሽ) በዛሬዋ ዕለት የተሰበሰብነው ያለምክንያት አይደለም ለአንድ ዐቢይ ቁም ነገር ነው ። ከ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ጀምሮ ቅድስት ቤተ ክርስቲ ያናችን እናትና አባት ሆና የቁመት የጥበብና የመ ንፈስ ዕድገትን በመስጠት ካሳደገቻቸው ወጣቶች መካከል አሥራ አንዱን ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ተቀብሎ በእትመት ሥራ እንዲያሠለጥናቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢት ዮጵያ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ/ም በማዘዛቸው ነው ። በዚህም ምክንያት የትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ትም የቅዱስነታቸውን አባታዊ ትእዛዝ በክብር ተቀብሎ የማተሚያ ቤቱ አስተዳደር የየክፍል ኃላ ፊዎችና ሠራተኞቹ በመተባበር ፲፩ ወጣቶች ለሁ ለት ዓመት አሠልጥኖ እነሆ በዛሬው ዕለት ለማስ መረቅ በቅዱስነታቸው መንፈሳዊ ገጸ ረድኤት እቅ ርበናል ። ሠልጥነው ለምረቃ ከቀረቡት ፲፩ ወጣቶች መካከልም ሰባቱ ሴቶች ሲሆኑ አራቱ ወንዶች ናቸው ። ከነዚህም ሌላ በቅርብ የተላኩ ሁለት ሴቶች ወጣቶች በመሰልጠን ላይ ናቸው ብለዋል ።

ሊ/ብርሃናት ሰሎሞን ንግግራቸውን በማራዘም ወጣቶቹ በልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ሥራ መሠልጠናቸውን ጠቅሰው ሰለጠኑ ስንል የአካዳሚክ ትምህርታ ቸው እንዳይቋረጥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ መምሪያ ታላቅ ጥንቃቂ ተደርጎላቸው ግማሽ ቀን እየተማሩ ግማሽ ቀን ደግሞ በማ/ቤቱ እንዲሠለጥኑ ተደርጎ ነው ።

ሀገራችን በኅብረተ ሰብአዊነት እንድትመራ አዲሱ ዲሞክራሲያዊ መርሐ ግብር ከአብዮታዊ መንግሥት ከተሰጠ ወዲህ በመላዋ ኢትዮጵያ የጭ ቁኖች ልጆች አስተዳደግ ትኩረት ተሰጥቶት እያበ በና እያፈራ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችንም የበኩል ዋን ድርሻ በመውሰድ በመላዋ ኢትዮጵያ የሕፃናት አስተዳደግ መርሐ ግብርን ዘርግታ እየተንከባከበች ማሳደግዋ እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው ።

የቤ/ክርስቲያናችን ዋና ሥራ ይህ እንደመሆኑ መጠን ለዚህ ሥራ የታደሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ናቸው ። ለዚህም ምስክሮቹ የዛሬዎቹ ተመራቂዎችና የተግ ባሩ ተመልካቾች ሁሉ ናቸው ። ይህ እርምጃ ለተ መልካች ሁሉ እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው ። የቅዱስነታቸው መልካምና አባታዊ አስተሳሰብ የዘ መኑን የሰው ልጆች ችግር ማቃለያ የሚረዳ በመንግ ሥትም ጥረት እየተደረገበት ያለ አስተሳሰብ ነው ። ብዙዎች ወጣቶች የአካዳሚ ትምህርትን እስከ ፲፪ኛ ክፍል ድረስ ይማሩና ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ሳይችሉ ሲቀሩ ሥራ ፈቶች በመሆን ከፍተኛ ችግር ይደርስባቸዋል ።






ቅዱስ ፓትርያርኩ ለተመራቂዎቹ የምስክር ወረቀት በሰጡበት ወቅት

የቅዱስነታቸው መልካም ሐመለካከት ቤ/ክር ስቲያን እንደ እናት ቅዱስ ፓትርያርኩ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደራቤነት እንደ አባት ሆነው የሚያሳድጉአቸው ልጆች የአካዳሚክ ትምህርት ብቻ ተምረው በኋላ ችግር እንዳይደርስባቸው በማሰብ የዘ መኑ ቴክኖሎጂ ካፈራው የቤ/ክርስቲያናችን ድር ጅት በሆነው ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት እን ዲሠለጥኑ ልዩ አባታዊ ትእዛዝ ሰጥተዋል ። እዚህ ዛሬ የሚመረቁት ወጣቶች በአካዳሚክ ትምህርታ ቸው ፲ኛና ፲፩ ክፍል የደረሱና በመማር ላይ ያሉ ና ቸው ቅዱስ አባታችን በሚያዙላቸው የሥራ መስክ ተሠማርተው ማታ ማታ በመማር ፲፪ኛን ክፍል መፈጸም እንደሚችሉ አንጠራጠርም «የሚል ይገኝ በታል ።


የሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ ንግግር በዚህ እንደ ተጠቃለለም አቶ ጸጋዬ በርሄ የኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ኃላፊ የሕፃናት አስተዳደግ ድርጅት በ፲፱፻ ፷፯ ዓ/ም እንደተቋቋመና በመጀመሪያም በወሎ ክፍለ ሀገር በረሀብ ምክንያት አባት እናታቸው የሞቱባቸው ሕፃናት አሰባስቦ ሥራውን እንደጀ መረ ከዚያም በየጊዜያቱ በችግርና በልዩ ልዩ ምክ ንያት አሳዳጊ ያጡትን ሁሉ እየሰበሰበ እንደሚያ ሳድግ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስም እንዳስመረቀ አጠር ያለ መግለጫ ሰጥተዋል ።

ከዚህም በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይ ማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ለወጣቶቹ የምስ ክር ወረቀት ከሰጡ በኋላ መሪ ቃል አሰምተ



ከተመራቂዎቹ ወጣቶች በከፊል

www.ethiopianorthodox.org



ተመራቂዎቹ ወጣቶች በምረቃው ዕለት

ዋል።» ከተናገሩትም ውስጥ ለበጎ ሥራ በተዘጋጀው የስብከተ ወንጌል አዳራሽ በዚሁ ወቅትም ለበጎ ሥራ እንድንሰበሰብ ላበቃን አምላክ ክብር ምስ ጋና ይግባው ቀደም ባሉት ዘመናት አባትና እናት የሞቱባቸው ብዙ ሕፃናት ሰብሳቢና ተንከባካቢ አጥተው በዕውቀትና በረሀብ ሥጋ ተቸግረው ከገጸ ምድር እንደጠፉ ሁላችንም እናውቃለን እንደዚሁም ከድሆች ቤተ ሰብ ተወልደው ማሳደጊያና መማሪያ አጥተው በከባድ ችግር ሲሰቃዩ የነበሩት ሁሉ አባት እናት አጥተው ከሞቱት ተለይተው አይታዩም ።

ባሁኑ ጊዜ ግን አባት እናት የሞቱባቸውም ሆኑ ከድሀ የተወለዱት ሁሉ መንግሥት በጥሩ እንክብካቤ ስለሚያሳድጋቸውና ስለሚያስተምራቸው በጣም የሚያስደስት ሆኖ ይታያል ። በይበልጥ ደግሞ ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነቱ እንክብካቤ እያደገ ሲሄድ እጅግ በጣም የሚያስደስት ዘመን እንደሚሆን እና ምናለን ።

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት የሠለጠኑ ወጣቶችም በዚሁ ዕድል ውስጥ ናቸው ይልቁንም ለወደፊቱ በሰ ለጠኑበት ዕውቀት ሠርተው ሲጠቅሙና ሲጠቀሙ ስናይ የበለጠ ደስታና ኩራት ይሰማናል ። ስለሆ ነም ከዛሬ ጀምሮ በሠለጠኑበት በትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ተቀጥረው እንዲሠሩ ፈቅጃለሁ» ብለዋል ። በዚሁም ጊዜ ወጣቶቹ የተሰማቸውን ደስታ በቅዱ ስነታቸው ፊት ቀርበው ገልጸዋል። በመጨረሻም በቅ ዱስነታቸው ምዕራን ጸሎት የበዓሉ ፍጻሜ ሁኖአል።

# የጠ/ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በጎንደርና በጎጃም አህጉረ ስብከት የሥራ ጉብኝት አደረጉ ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ከኅዳር ፩ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ጀምሮ ለአሥር ቀናት ያህል በጎንደርና በጎጃም አህጉረ ስብከት እየተዘዋወሩ በርእስ ከተ ማዎች በአውራጃዎችና በወረዳዎች የሚገኙትን ፤ የልማት ሥፍራዎች የመንፈሳዊ አዳሪ ቤቶችንና በባ ሕር ዳር ከተማ የተቋቋመውን የጎንደርና የጎጃም የካህናት ማሠልጠኛ ማእከል እንዲሁም ታሪካውያን ገዳማትንና አድባራትን በመጎብኘት ለተቋቋሙት የልማት መዋቅሮች የማበረታቻ ምክርና የሥራ መመ ሪያ ሰጥተዋል ።

ዋና ሥራ አስኪያጁ በሁለቱ አህጉረ ስብከት የሥራ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ብፁዕ አቡነ መቃ ርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፤ ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፤አቶ በርሄ በየነ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መም ሪያ የዕቅድና የሥራ አመራር አማካሪ እንዲሁም ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና የየአህጉረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች ተገኝተዋል ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በጎንደር ሀገረ ስብከት ባደረጉት የሥራ ጉብኝት በሊቦ አው





ዋና ሥራ አስኪያጁ በጎንደር ከተማ የሀገረ ስብከቱን እንቅስቃሴ ሲመለከቱ

ራጃ በአብናት ወረዳ የሚገኘውን የምሥራቅ ጎንደር ንና የምዕራብ ወሉን የርዳታ ማስተባበሪያና የመ ልሶ ማቋቋም ጣቢያ በመጎብኘት የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጣቢያው ለሚገኙት ችግረኞች ከአሁኑ በፊት ካደረገችው የገንዘብና የማ ቴሪያል የቁሳቁስ ርዳታ ሌላ ወደፊትም አቅሟ በሚ ፈቅደው መሠረት ከመንግሥት ጎን በመሰለፍ ችግ ረኞቹን ለመርዳት ዝግጁ መሆኗን አስረድተዋል ።

ለሥራ ጉብኝቱ በወጣው መርሐ ግብር መሠ ረት ዋና ሥራ አስኪያጅ የመጀመሪያ ጉብኝት በ፲፩ ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተተከለችውንና በጎንደር ዙሪያ አውራጃ የምትገኘውን ጥንታዊቷን የጎርጎራ ደብረ ሲና ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ባህል ሚኒስቴር ታሪካውያን ሥፍራዎችን ለማሳደስና ለማ ስከበር ባለበት ኃላፊነት እሷንም በአስደናቂ ሁኔታ እድሳቷ በአሁኑ ጊዜ በዘመናዊ ቅርጽና ይዘት ላይ ስለምትገኝ ባህል ሚኒስቴር ሊመሰገን ይገባዋል ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ከዚህ ጉብኝ ታቸው በኋላ ከአሁኑ በፊት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ እርሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የጎንደርን ሀገረ ስብከት በጐበኙበት ወቅት ለገዳማቱና ለአድባራቱ መርጃ ይሆን ዘንድ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይ ነት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት የርዳታ ሰጪ ክፍ ሎች ተጠይቆ ሁለት ዘመናዊ የሀል ወፍጮ በሀገረ ስብከቱ ርእሰ ከተማ እንዲተከል ባዘዙት መሠረት በጎንደር ርእሰ ከተማ በአቡን ገብርኤል ቤተ ክርስ ቲያን ቅጽር ግቢ ተተክሎ ሥራውን በመጀመር ላይ የሚገኘውን ሁለት ዘመናዊ የሞተር የሀል ወፍ ጮና በዘመናዊ መልክ አዲስ የተሠራውን የሀገረ ስብከቱን ጽ/ቤት እንዲሁም በጎንደር መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ/ገረገራ ውስጥ የተቋቋመውን የአልባሳት ስፌትና የቆዳ ሥራ ድር ጅትን በተጨማሪም በምእመናን አስተዋጽኦ በ፩፻፴ ሺህ ብር በዘመናዊ አሠራር የተሠራውን ጥንታዊ ውን የአደባባይ ኢየሱስን ቤተ ክርስቲያንና የሐዋ ርያው ቅዱስ ጳውሎስን መንፈሳዊ አዳሪ ቤትን አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ።

ዋና ሥራ አስኪያጁ የሐዋርያው ቅዱስ ጳው ሎስ መንፈሳዊ አዳሪ ቤትን በጎበኙበት ጊዜ የመን ፈሳዊ አዳሪ ቤት ሕጻናት ተማሪዎች መንፈሳዊ መዝሙር እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል ። ከዚህም ጋር አቶ ሞገስ ገብረ ዋሕድ የመንፈሳዊ አዳሪ ቤቱ ርእሰ መምህር በጉብኝቱ የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ የአዳሪ ቤቱን አቋምና ይዞታ አስረድተዋል ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በዚሁ ጊዜ ለሕጻናት ተማሪዎች በሰጡት ምክር ሕጻናት በትም ህርትና በአካል በእንክብካቤ ማደግ እንደሚገባ ቸው በመግለጽ የነገይቱ ኢትዮጵያ መሪዎች ሊሆኑ የሚችሉት የዛሬዎቹ ሕጻናት ስለሆኑ ከአሁኑ ሰው የተሻለ ሰው ሆኖ ለመገኘት በትምህርትም ታንጸ እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል ።

ዋና ሥራ አስኪያጁ ምክራቸውን በመቀጠል መድኃኒታችን ክርስቶስ «ሕጻናትን ተውአቸው ፤ ወደእኔ ይመጡ ዘንድ የሙት ልጆች እንድትሆኑ



www.ethiopianorthodox.org

አልተዋችሁም» ብሎ በተናገረው መሠረት በትግራቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የማትዘነጋቸውና ከጎናቸው የምትቆም መሆኗን ጠቅሰው በሥራልና በግብረገብነት እንዲሁም በታማኝነትና በቆራጥነት ያለፉት አባቶታቸውን አርአያ እንዲወርሱ በማስገንዘብ የወደፊት የፖለቲካ ሰዎችንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማፍራት የሚቻለው ከሕጻናት መካከል ስለሆነ በትምህርትም ሆነ በዕድሜ የበሰሉት ሕጻናት ተማሪዎችን እንዲረዱአቸውና እንዲቈጣጠሯቸው አሳስበዋል ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አዳሪ ቤት በባዕድ እጅ ተይዞ ሲኖር ከለውጡ ወዲህ ማንኛውም ተቋም በተጎናጸፈው ብሔራዊ ጸጋ የተገኘው በብዙ መሥዋዕትነትና ጥረት መሆኑን አውስተው ሌሎች እንደሚያደርጉት የአካባቢው ኗሪ ሕዝብ ተረጅ ሕጻናትን ተንከባክቦ የማሳደግ ግዴታ ያለበት መሆኑን ማሳወቁ የመምህራኑና የሥራ ኃላፊዎቹ ግዴታ መሆኑን በመጥቀስ ሕጻናት ተማሪዎቹ ከመንፈሳዊው ተልእኮ ተሳትፎአቸው ጋር የመንግሥትን መመሪያ በማክበር በአኢወማ እየተመዘገቡ የብሔራዊው አገልግሎት ተሳታፊዎች መሆኑንም እንደሚገባቸው በመግለጽ በሚደርስባቸው ችግር ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የተቻላትን ያህል ርዳታ ከማድረግ እንደማትቆጠብ አስረድተዋል ።

ከዚህ በኋላ በብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የማሳረጊያ ጸሎት ተደርጎ የመንፈሳዊ አዳሪ ቤቱ ጽ/ቤት የተማሪዎቹ የመኝታ ክፍሎችና የምግብ አዳራሽ አንድ በአንድ ተጎብኝቷል ።

ቀጥሎም ከጎንደር ርእሰ ከተማ ፩፻፵ ኪ/ሜ ርቆ በሊቦ አውራጃ በአብናት ወረዳ ወደሚገኘው የርዳታ ማስተባበሪያና የመልሶ ማቋቋሚያ ጣቢያ በማምራት በመጀመሪያ በሊቦ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት ተገኝተው ከአውራጃው አስተዳዳሪ ከጓድ ፍትአለው ደምስ ጋር በምሥራቅ ጎንደር ስለደረሰው ችግርና ስለጉብኝቱ ከተወያዩ በኋላ ጉዞአቸውን ወደ ርዳታ ማስተባበሪያ ጣቢያው ቀጥለው ከሥፍራው እንደደረሱ በጓድ ወርቅነህ ተገኝ የአብናት ወረዳ አስተዳዳሪና በጓድ ታምሩ አበራ የርዳታ ማስተባበሪያው ጣቢያ ኃላፊ አማካይነት የመጠለያ ጣቢያውን አንድ ባንድ እየተዘዋወሩ በጎበኙበት ወቅት የጣቢያው ኃላፊ የችግሩን መንሥኤና የችግረኞቹን ሁኔታ ጠቅሰው በአሁኑ ጊዜ ችግሩ በመቃለል ላይ መሆኑንና ለችግሩም መቃለል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም በጎ አድራጊ ድርጅቶች ከፍተኛ የገንዘብና የማቴሪያል የቁሳቁስ ርዳታ ማድረጋቸውን በቃርት በተደጋጋሚ ማስረጃ አስገንዝበዋል ።



ከዚያም ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ባደረጉት መልስ ንግግር የጣቢያው ኃላፊዎች ለሥራው የሚከፍሉት መሥዋዕትነት ቀላል አለመሆኑን በመጥቀስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይነት ከዚህ በፊት ካደረገችው ብር ፩፻፹ ሺህ የቁሳቁስ ርዳታ ሌላ ወደፊትም በአስፈላጊው ርዳታ ሁሉ ለመተባበር ዝግጁ መሆኗን ቃል ከገቡ በኋላ የችግረኞች መጠለያ ጣቢያዎችን የቀይ መስቀል የሕክምና ክፍሎችን የምግብ ማከማቻ አዳራሾችንና መጋዝኖችን ሌሎችንም የጣቢያው የአገልግሎት ፤ መስጫ ክፍሎችን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል ።

ከዚህ በኋላ ወደ ወረታ በማምራት በሰሜን ዞን የመንፈሳዊ አዳሪ ቤቶች ኃላፊና ተቆጣጣሪ በሆኑት በአቶ ወርቁ ሽፈራውና የወረታ መንፈሳዊ አዳሪ ቤት ጸሐፊ በሆኑት በወ/ት ፀሐይ መለሰ አማካይነት በወረታ ከተማ የሚገኘውን መንፈሳዊ አዳሪ ቤትን ጎብኝተዋል ። በጉብኝቱም ወቅት የአዳሪ ቤቱን ጽ/ ቤት የመኝታ ክፍሎችንና የምግብ አዳራሹንም እንዲሁም የዕቃ መጋዘኑን ተዘዋውረው በመመልከት ለተማሪዎቹ የማበረታቻ ምክር ሰጥተዋል ።

በዚሁ ዕለት ከጎንደር ከተማ ፩፻፰ ኪ/ሜ ርቀት ላይ ወደ ሚገኘው ወደ ደብረ ታቦር አውራጃ በማምራት ከርእሰ ከተማው እንደደረሱ የደብረ ታቦር መንፈሳዊ አዳሪ ቤት ተማሪዎችና መምህራን በመዝሙርና በቅኔ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ባደረጉትም የአቀባበል ሥነ ሥርዓት የአዳሪ ቤቱ ርእሰ መምህር በሆኑት በአቶ ጎይአቶም አብርሃም ስለ አዳሪ ቤቱና ስለ አቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ቅደም ተከተል መግለጫ ከተሰጠ በኋላ ሦስት መዘምራን «ተዘከር እግዚኦ ከመመሬት ንህነ» የሚለውንና እንዲሁም «ኢይትአጸዉ አናቅጽኪ ውእቱ ከብርሙ ለካህናት ሊቀ ማእምራን አሠርገዋለቤተክረስቲያን» የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር በደብረ ታቦር ኢየሱስ አስተዳዳሪ በመልአከ ታቦር ልብሰ ወርቅ ገሠሠ መሪነት በጣዕመ ዜማ ዘመሩ ።

ከዚሁ በማያያዝ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጉብኝቱን ዓላማ በመጥቀስ በተደረገላቸው መንፈሳዊ አቀባበል የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል እንዲሁም ሁሉም ዜጋ ከሀገሪቱ ሕግ በታች መሆኑን በማስገንዘብ ነገ ኢትዮጵያን በተሻለ ሁኔታ ለመምራት የመንግሥት መመሪያዎችን አክብር ትምህርትን በትጋት መማር የማንኛቸውም ተማሪዎች ድርሻ መሆኑን አውስተው ከዚህ ዓላማ ውጭ በተማሪዎቹ ለመነገድና ለመጠቀም የሚሞክር ካለ ቤተ

ክርስቲያን አጥብቃ የምትቃወም መሆኗን አስገንዝበዋል ።

በተጨማሪም ዘመናዊ ትምህርት ሊገኝ የቻለው በጥንታዊው ትምህርት መሠረትነት ስለ ሆነ መንፈሳዊውን ትምህርት ማክበር እንደሚገባቸው ጠቅሰው የመንፈሳዊ አዳሪ ቤት ተማሪዎች በወላጆቻቸው ቤት ሆነው የቤት ሥራ እየሠሩ እንደሚማሩ ተማሪዎች ድርብ ኃላፊነት ስለሌለባቸው በትምህርታቸው የበለጠና የተሻለ ውጤት እንደሚጠበቅባቸው አስረድተዋል ።

በደብረ ታቦር ርእሰ ከተማ በተደረገው የሥራ ጉብኝት በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኙ ትን አድባራትንና የሚያገለግሏቸውን ካህናት ይረዳ ዘንድ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይነት በመሃል ከተማው ተተክሎ በሥራ ላይ የሚገኘውን ዘመናዊ የሞተር የህል ወፍጮ ከመጎብኘታቸውም በላይ ከ፺፻፵ ዘመን በላይ ዕድሜ ያለውንና በአጼ ሠይፈ አርዕድ ጊዜ የተተከለውን ታሪካዊውን የደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንንና በታሪካዊነቱ ተወዳዳሪ የሌለውን የደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተዋል ።

ከዚያም ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ከደብረ ታቦር ከተማ ፸፰ ኪ/ሜ ርቆ ወደሚገኘውና የጋይንት አውራጃ ርእሰ ከተማ ወደሆነው ወደ ነፋስ መውጫ አምርተው በዚያ የሚገኘውን የመንፈሳዊ አዳሪ ቤት በመጎብኘት ለተማሪዎቹ የማበረታቻ ምክር ከመስጠታቸውም ሌላ የአዳሪ ቤቱን የመኝታ ክፍሎችና የምግብ አዳራሹን ተዘዋውረው ተመልክተዋል ።

በዚህም ወቅት የአዳሪ ቤቱ ርእሰ መምህር የሆኑት ቄስ አንዳርጌ መኰንን የአዳሪ ቤቱን አቋምና ይዞታ ከመግለጽ ጋር ልዩ ልዩ ቅኔዎችን አበርክተዋል ። ተማሪዎችም «እንኳን ደህና መጣችሁ» የሚለውን መዝሙር በመዘመር አቀባበል አድርገዋል ።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በጎንደር ሀገረ ስብከት የሚያደርጉትን የሥራ ጉብኝት ፈጽመው ወደጎጃም ሀገረ ስብከት በማምራት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ መሪነት ጉብኝታቸውን ቀጥለው ሁለት ሰዓት ተኩል



ሥራ አስኪያጁ ጣና ደሴት ውስጥ ወደሚገኘው ዳጋ እስጢፋኖስ በጀልባ ሲጓዙ ።

የደብረ ታቦር ኢየሱስ አቀማመጥ በምሥራቅም ሆነ በምዕራብ በሰሜንም ሆነ በደቡብ በጠቅላላው በአራቱ ማዕዘናት የሚገኙትን የአዋሳኝ አገሮች አድማሳት ቁልጭ አድርጎ ስለሚያሳይና እንደሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በዚያው ቤት ሠርተ መኖርን የሚያስመኝ ስለሆነ እውነትም ደብረ ታቦር ብለናል ።

በሚፈጀው የጀልባ ጉዞ የጣናን ሐይቅ አቋርጠው ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በመጓዝ ለገዳሙ መርጃ ይሆን ዘንድ በገዳሙ ማኅበር መነኮሳት ኃላፊነት በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይነት የተተከለውን ዘመናዊ የሞተር የህል ወፍጮ ጎብኝተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ዘመናዊው የሞተር ወፍጮ ለደቅ ደሴት ኗሪ ዎችና ለአካባቢው የገበሬ ማኅበር ከፍተኛ ጥቅም በመስጠቱ «ኀየንት» ወይም አረፈ ሴቱ ተብሎ መሰየሙን የገበሬ ማኅበር ሊቀ መንበሩ ጓድ ይህ ዓለም ገብረ ማርያም ገልጸዋል ።

በሞተር ወፍጮው የሚረዱት በደቅ ደሴት ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ዝርዝር ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

፩/ ናርጋ ሥላሴ
፪/ ቆላ አርሰማ
፫/ ዝብድ ኢየሱስ
፬/ ኮታ ማርያም
፭/ ጋደና ጊዮርጊስ
፮/ ጀጋ ዮሐንስ
፯/ ወባ አዳሁናት (ምሕላ ኪዳነ ምህረት ሲሆኑ ሞተር ወፍጮው እነዚህን ሁሉ የሚመግብና አካካ ዳካማውን ጨምሮ በአካባቢው የሚኖረውን ፯፻ ሕዝብ የሚረዳ መሆኑን የገበሬ ማኅበር ሊቀ መንበሩ ጨምረው ገልጸዋል ።

የሞተር ወፍጮው የሚንቀሳቀሰውና ሥራውን የሚያከናወነው ከገዳሙ የአንድነት ማኅበር በተወከሉ መነኮሳት ጉልበት መሆኑን በሥራው ከተጠመዱት አንዱ አባ አትዓለማ እሸቱ ገልጸዋል ። እኛም በዓይን ተመልክተናል ።

ቀጥሎም ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አምርተው የገዳሙ መነኮሳት ያለሙትን የእርሻ ሰብልና የልዩ ልዩ አትክልት ልማት ሥፍራ ተመልክተዋል ። የገዳሙ መነኮሳት ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጎጃምን ክፍለ ሀገር በጎበኙበት ወቅት ባደረጉላቸው የገንዘብ ርዳታ የውሃ ሞተር ገዝተው የልማት ቦታዎችን በማጠጣት የሚጠቀሙ መሆናቸውን ከምስጋና ጋር ገልጸውልናል ።

በአጠቃላይ የገዳሙ መነኮሳት ከጸሎታቸውና ከትሩፋታቸው ጋር የሚጠቀሙት በእርሻ ነው ። ንቃታቸውና ትጋታቸው ለሌላው የገበሬ ማኅበር አርአያነት አለው የከተማ መነኮሳት ይህን የተቀደሰ አርአያ መከተሉና እንዲህ ወደ አለው የሥራ መስክ ተሰማርተው ኅብረተሰቡን በማገልገል ነፍሳቸውንም ሆነ ሥጋቸውን ቢጠቅሙ ምንኛ ጥሩ ነበር ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የዳጋ እስጢፋኖስን ገዳም በጎበኙበት ወቅት የቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታትን ማለት ፤

፩/ የአጼ ዳዊትን
፪/ የአጼ ፋሲልን
፫/ » ሱስንዮስን
፬/ » ዘርዓ ያዕቆብን አጽም ከክብር ልብሳቸውና በዘመኑ ከነበረው የወግ ዕቃቸው ጋር ተመልክተዋል ። ሌላውንም የገዳሙን የውስጥ ድርጅት በገዳሙ አበምኔት በመምህር ክፍለ ማርያም መንግሥቱ አማካይነት ጎብኝተዋል ለነገሥታቱ አጽም የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ከፍተኛ እንክብካቤ ስለአደረገለት ሊመሰገን ይገባዋል ።

በዚህም ጊዜ ጓድ ሊቀ መንበር ባደረጉላቸው የገንዘብ ርዳታና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ለገዳሙ የሞተር ወፍጮ በማስገባት ባደረጉላቸው ከፍተኛ ድጋፍ የአንድነት ገዳም መነኮሳት የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ለዚሁ በጎ አድራጎት የተለመደ የዘወትር ጸሎታቸውን የማያቋርጡ መሆናቸውን አባ ወልደ ሚካኤል የተባሉት መነኩሴ መነኮሳቱን በመወከል ተናግረዋል ።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ታሪካዊውን ቦታ በመጎብኘት የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ አገር የምትጠበቀው በሌላ ኃይል ብቻ ሳይሆን በመናንያን ጸሎት ጭምር መሆኑንና መነኮሳትም በጸሎትና በተባሕትዎ የሚደክሙት ላራሳቸው ብቻ ሳይሆን ሌላውን ይዞ ለመጽደቅ መሆኑን ጠቅሰው ለዚህ ዓይነት ታሪካዊ ሥፍራ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ርዳታ ከማድረግ እንደማትቦዝን ግልጸው ለገዳሙ አንድ የአበባ ምንጣፍ ለመስጠት ቃል ገብተዋል ።

ከዚሁ በማያያዝ አቶ በርሄ በየነ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የዕቅድና የሥራ አመራር አማካሪ በገዳሙ ታሪካዊነትና በመነኮሳቱ የልማት ሥራ የተደሰቱ መሆናቸውን በመግለጽ ለዚሁ ዓይነቱ የልማት ሥራ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ መንገድ ካገኘ ለመርዳት ወደ ኋላ እንደማይል አስገንዝበዋል ።

በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቦታውን ታሪካዊነት ጠቅሰው ያለፉትም ሆነ የአሁኑ መሪዎች ለቦታው ያላቸውን መንፈሳዊ ስሜት በመግለጽ የጠቢብ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና ሌሎችም የሥራ ኃላፊዎች ያላቸውን እንገብጋቢ የሥራ ጊዜ ሰውተው ጉብኝት በማድረጋቸው ሊመሰገኑና የጎደለውን እንዲያሟላላቸው ጸሎት ማድረግ እንደሚገባ በማውሳት በየገዳማቱ ፳፬ ሰዓት ሙሉ ለጸሎት የሚተጉ አበው ስለአሉን እኛም ጠቅላላ ኅብረተሰቡ የሚጠበቀው በእነሱ ጸሎት ነው ። » በማለት የማሳረጊያ ጸሎት አድርገው ዋና ሥራ አስኪያጁ ወደ መሃል ዘጌ ገዳም ጉብኝታቸውን ቀጠሉ ።

ከዚያም በኡራ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ክልል ውስጥ የሚገኙትን ፤

፩/ ኡራ ኪዳነ ምሕረትን
፪/ አዝዋ ማርያምን
፫/ ኡራ ሥላሴን
፬/ መሃል ዘጌ ጊዮርጊስን
፭/ መሃል ዘጌ ቤትረ ማርያምን
፮/ ይጋንዳ ተክለ ሃይማኖትንና
፯/ ፉሩ (ፍሬ) ማርያምን እንዲመግብ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይነት በመሃል ዘጌ የተተከለውን የሞተር ወፍጮ ጎበኙ በዚሁ መሪጌታ ፈለገ ጥበብ አንዱ ዓለም የገዳሙን መነኮሳትና የአካባቢውን ተጠቃሚ ሕዝብ በመወከል የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የሞተር ወፍጮውን በመለገሥ ባደረገው ርዳታ የአካባቢው ኅብረተሰብም ሆነ መነኮሳቱ የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል ።

ቀጥሎም ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ወፍጮው ሊተከል የቻለው በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አሳሳቢነትና ጥረት መሆኑን ጠቁመው ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ኅብረተሰቡን በመገልገል በኩል የተለየ ዓላማ እንደሌላቸው በመግለጽ ወደፊትም ከመንግሥት ጎን በመሰለፍ ቤተ ክርስቲያን ባላት አቅም ኅብረተሰቡን ለመርዳት ዝግጁ መሆኗን አስረድተው ለመነኮሳቱም ሆነ ለጠቅላላው ኅብረተሰብ የማበረታቻ ምክርና የሥራ መመሪያ ሰጥተዋል ።

የሞተር ወፍጮው የሚያገለግለው ከገዳሙ ሌላ ሁለት የገበሬ ማኅበር ሲሆን በጠቅላላው ከ፫ሺ ያላነሱ ሕዝብ የረዳ ከመሆኑም በላይ አንድ በዓመት ውስጥ ያስገኘው ገቢ ከተገዛበት ዋጋ እጋማሽ በላይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል ። ከተገኘውም ገቢ ውስጥ በተሰጠው መመሪያ መሠረት የኡራ ደብረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እንደታደሰበትና ለሞተር ወፍጮው የሚያገለግል መጋዘን እንደተገዛበት ተመልክተናል ። በእውነቱ የመሐል ዘጌ የሞተር ወፍጮ የሥራ ይዞታ ለሌሎችም መልካም አርአያነት ያለው ነው ።

በዚሁ ወቅት ባልታወቀ ምክንያት የእሳት አደጋ ስለደረሰባት ተቃጥላ አቶ አምባው ዓለሜ በ ተ ባ ሉ በጎአድራጊ ግለሰብ አማካይነት አዲስ በመሠራት ላይ ያለችውን የፍሬ (ፍሬ) ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተዋል ። ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ቤተ ክርስቲያኑን ለማሠራት በግል ገንዘባቸውና ጥረታቸው ያስጀመሩትን በጎ አድራጊ በማመስገን የማበረታቻ ምክር ሰጥተዋቸዋል ። የሀገረ ስብከቱ ድጋፍ እንዳይለያቸው በማሳሰብ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በተቻለ መጠን ለመርዳት ወደ ኋላ እንደማይል ተናግረዋል ። በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አዲስ በመሠራት ላይ ያለውን የቤተ ክርስቲያኑን ጅምር ባርከው የማሳረጊያ ጸሎት ካደረጉ በኋላ በዳጋ እስጢፋኖስ ና በመሐል ዘጌ ገዳም የሚደረገው የሥራ ጉብኝት ፍጻሜ ሆኗል ።

በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ጉብኝት የሚጠቆም ነገር ቢኖር ቦታው እንዲያ ሳለ ታሪክና ምዕራፈ ቅዱሳን መሆኑ እየታወቀ ለቱሪስቶቹም እጅግ አመቺ ሥፍራ ቢሆን ቤተ ክርስቲያኑ ከዚህ ግባ የማይባል ሰቀላ ቢጤ ከመሆኑም በላይ በዘመን ብዛት ተሰነጣጥቆና እነግንጎ በመፍረስ ላይ ስለሆነ ሀገረ ስብከቱ ጠቅላይ ቤተ ክህነትንም ሆነ ሌሎች በጎ አድራጊ ድርጅቶችንና ባሕል ሚኒስቴርን በማሳሰብ ራሱም የተቻለውን ያህል በመጣር እንዲታደስ የማድረግ ኃላፊነት አለበት ።



ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በባሕር ዳር የካህናት ማሠልጠኛ የልማት እንቅስቃሴ ሲመለከቱ



www.ethiopianorthodox.org

ቀጥሎ የተጎበኘው የጎጃምና የጎንደር አህጉረ ስብከት ማዕከል የሆነው የባሕር ዳር የካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤትና የማሠልጠኛው የልማት ሥፍራ ሲሆን በእውነቱ የማዕከሉን ቅጽር ግቢ ሲመለከቱት አዲስ በመቆርቆር ላይ ያለ አንድ አነስተኛ ከተማ ይመስላል ። የፓፓየው ፤ የቡናው ፤ የበንኮራውና የመሳሰለውም የአትክልት ሰብል ሲመለከቱት ያስገርማል ።

ይህ ሁሉ የልማት ሥራ ሊስፋፋ የቻለው በሀገረ ስብከቱ ብርታትና ጥረት በሁለት የውሃ ሞተር ተጠልፎ የጣና ሐይቅ ስለሚያጠጣውና ለሥራ ትኩረት ስለተሰጠው መሆኑን ተረድተናል ። ከዚህም ጋር የላሞች ርቢ ያስደስታል ወይን ተክሉ ፍሬውን የማይበላ መንጋስ ጠብቆ (አርብቶ) ወተቱን የማይጠጣ ማነው? ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባስተማረው መሠረት ከፍሬውም ከወተቱም ቀምሰንለታል ።

በማሠልጠኛው ቅጽር ግቢ ከዘመናዊው የሥልጠና ትምህርት ጋር ጥንታዊውም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጎንለጎን ስለሚሰጥ ከአትክልቱና ከልዩ ልዩ የሰብል ምርት ያላነሰ የቅኔ ምርት ቀርቦልናል ። እንደ በዓለ ሃምሳ ትንሹም ትልቁም በልሳን ይናገር ስለነበር እኛም በተመስጦ ለመዝረፍ ሞክረን ነበር ። በያሬዳዊው መዝሙር በኩልም የቀረበልን ገጸ በረከት የዚያኑ ያህል ነበር ። በጠቅላላው የባሕር ዳሩ የካህናት ማሠልጠኛ ማዕከል ለሌሎች የካህናት ማሠልጠኛ ማዕከላት መልካም አርአያነት ያለው ነው ። ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም ።

ታዲያ ለዚህ መልካም ምሳሌነት ላለው የካህናት ማሠልጠኛ ማዕከል አንድ ቤተ መጻሕፍት ስለሚያስፈልገው ቤተ መጻሕፍት ለመሥራት መሠረቱ ተጀምሯል ። ነገር ግን ርዳታ እንደሚያስፈልገው ሊቀ ጳጳሱ ገልጸዋል ። በዚያውም ላይ የካህናት ማሠልጠኛው ማዕከል ከጣና ሐይቅ ዳር በመሆኑ የጀልባ ርዳታ ቢያደርግለት እንደ ዳጋ እስጢፋኖስና እንደ ኡራ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የመሳሰሉትን የታሪክ ሥፍራዎችን ለመጎብኘትም ሆነ ለማሠልጠኛው ጥቅም እንደሚሰጥ ሊቀ ጳጳሱ አስረድተዋል ። እኛም ይደልዎ ብለናል ለሁሉም በተቻለ መጠን ርዳታ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ ሊቀ ማእምራን ቃል ገብተዋል ። ይልቁንም ቦታው ለቱሪስቶች አመች ስለሆነ ከቤተ መጻሕፍቱ ጋር የእንግዶች መዝናኛ ቤት ተጨምሮ እንዲሠራ መመሪያ ሰጥተዋል ።

በማሠልጠኛው ቅጽር ግቢ ያሉ የቅኔ ተማሪዎችና ረዳት ዘመድ የሌላቸው ተስፈኞች ስለሚኖሩ ለቤተ መጻሕፍቱ ማሠሪያና እነዚህን ለመሳሰሉት ተረጂዎች ሁሉ ተጨማሪ ርዳታ እንደሚያስፈልግ የማሠልጠኛው ርእሰ መምህር ዲያቆን ዘለዓለም ደስታ ገልጸዋል ። ዋና ሥራ አስኪያጁም ደረጃ በደረጃ ርዳታውን ለማድረግ እንደሚጥሩ ቃል ገብተዋል ።

በዚሁ ወቅት ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የባሕር ዳር መንፈሳዊ አዳሪ ቤትን በመጎብኘት ለአዳሪ ተማሪዎቹና ለመምህራኑ የማበረታቻ ምክር ሰጥተዋል ።

ከዚህ በኋላ የሥራ ጉብኝቱን ወደሞጣ አውራጃ በመቀጠል አዲስ በመሠራት ላይ ያለውን ፤ የሞጣ አውራጃ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትንና የአውራጃው መንፈሳዊ አዳሪ ቤትን ጎብኝተዋል ። በጉብኝቱም ወቅት ዋና ሥራ አስኪያጁ ለአዳሪ ተማሪዎቹና ለመምህራኑ የተለመደውን የማበረታቻ ምክር በመስጠት የአዳሪ ቤቱን የመኝታ ክፍሎችና የምግብ አዳራሹን እንዲሁም ጽ/ቤቱንና የአትክልቱን ሥፍራ ጎብኝተዋል ።

በመጨረሻም ወደ ዲማ ጊዮርጊስ በማምራት በታላቁና በታሪካዊው ገዳም በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይነት ተተክሎ በሥራ ላይ ያለውን የሞተር ወፍጮና ቤተ ክርስቲያኑን ጎብኝተው የማበረታቻ ምክርና የሥራ መመሪያ በመስጠት በጎንደርና በጎጃም አህጉረ ስብከት የሚደረጉትን ጠቅላላ የሥራ ጉብኝት ፈጽመው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ።

በሠረቱ ዋና ሥራ አስኪያጁ በጎንደርና በጎጃም አህጉረ ስብከት ባደረጉት የሥራ ጉብኝት በሁለት አህጉረ ስብከት የሚታየውን የሥራ እንቅስቃሴና እሽቅድድም በተለይም የጎጃምን ሀገረ ስብከት ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴ ስንመለከት ለቤተ ክርስቲያናችን የወደፊት ሕልውናና የአገልጋዮቹ ካህናት የተሻለ የኑሮ ዕድል ብሩሕ ተስፋ አሳድሮብናል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ባለፈው ጊዜ በጎንደርና ጎጃም አህጉረ ስብከት ያደረጉት አባታዊና በረከታዊ የሥራ ጉብኝትም ከፍተኛ ሐዋርያዊ ፍሬ እንዳያፈራ ለመገመት ችለናል ።

በተለይም በአብነት የእርዳታ ማስተባበሪያ ጣቢያ በተደረገው የሥራ ጉብኝት ቤተ ክርስቲያናችን ለችግረኞች በየጊዜው ያደረገችውን የገንዘብና የማቴሪያል ርዳታ በቻርት በተደገፈ ማስረጃ በተመለከትን ጊዜ ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን ከሆነ ጀምሮ በመቃብር ቤትና በደጀሰላም በሌሎችም የሰንበቴ ቤትን በመሳሰሉት የችግረኞች መርጃ ጣቢያዎች የችግረኞች ምጽላል ከመሆኗና ዕጓለ ማውታዎችን ከመታደግ የቦዘነችበትጊዜ ባይኖርም በአጠቃላይ የተቸገሩ ኀብረተ ሰቦች ሞግዚት ሆና መኖሯ ባይካድም በቅርቡ ሲሰነዘርበት ከነበረው አንድ አንድ ሐሜት ነጻ ወጥታ በማየታችን የተሰማን ደስታ ወሰን የለውም ።



በጠቅላላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በኅብረተሰቡ ጎን በመሰለፍ የምታበረክተውን ሥጋዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ሲመለከቱት ቀድሞ አብዮት ካደረጋቸው የዘመናት የሥራ ታሪክ ድኅረ አብዮት ማለት በ፲ ዓመት ውስጥ ያሳየችው የሥራ እንቅስቃሴ አመዝኖ ስለሚገኝ በዚሁ ብሩህ በሆነው ሐዋርያዊ የሥራ እንቅስቃሴ ከቀጠለች በቅርብ ጊዜ ራሷን እንደም ትችልና ለሌሎች እንደምትተርፍ መተንበይ አያዳግትም ለዚሁ ሁሉ ሐዋርያዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሥራው ከወረቀት ወደ ቢሮ እንዲመጣ ከመጠባበቅ ይልቅ ሠራተኞቹ ወደ ሥራው እንዲሄዱ ማድረግ ዋናው መፍትሄ ስለሆነ በየአህጉረ ስብከቱ ለተመደቡት የሥራ ኃላፊዎችም የሥራ መመዘኛ በመሆኑ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክም ሆነ በዋና ሥራ አስኪያጁ የሚደረገው የሥራ ጉብኝት ቢቀጥል ለሥራው እንቅስቃሴ የበለጠ ፍጥነትና ውጤት እንደሚሰጥ ይታመናል ።

የዜናው አቅራቢ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ.

# አጠቃላይ የሰበካ መ/ጉባኤ

በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀ መንበርነት የሚካሄደው ስብሰባ ከተሰየመበት ወዲህ ሁለት ጊዜ ጉባኤ አድርጎአል ።

ስብሰባው የተካሄደው ፩ኛ/ ሰኔ ፲፯/፲፱፻፸፰ ዓ/ም ፪ኛ ጥቅምት ፫ እና ፬ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ነው ። ጉባኤው የሥራ ርምጃው ለማጠቃለል ያመቸው ዘንድ ለጥቅምት ፯ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ቀጠሮ አድርጎ የዕለቱ ስብሰባ በጸሎት ፈጽሞአል ።

የዚህ ታሪካዊና የቤ/ክርስቲያናችን መዋቅር የሆነው ስብሰባ የተካሄደው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ/ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት በዋናው ሥራ አስኪያጅና የዚሁ ስብሰባ ሊቀ መንበር ቢሮ ነው ።

ይህ ታሪካዊና ለብዙ ዘመናት ሲጠበቅ የቆየው የቤ ክርስቲያናችን ጽኑ መሠረት በጸሎት እንደተከፈተ የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የዚሁ ጉባኤ ሊ/መንበር ሊ/ማእምራን አበባው ይግዛው ለጉባኤው የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል ።

ሊ/ማእምራን በንግግራቸው ጊዜ የሰጡት የቤተ ክርስቲያን ቀዋሚ መመሪያና ጠንካራ ሀሳብ ከየሀገረ ስብከቱ የመጣችሁ ፤ እንዲሁም ከመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት የተመረጣችሁ የዚሁ ታሪካዊ ጉባኤ አባላት በዚህ ታሪካዊ ስብሰባ ለመገኘት እንኳን ደህናመጣችሁ» ካሉ በኋላ« በቤ/ክርስቲያናችን ታላቅ ጉባኤ ባለአደራዎች ሆነን ይህን ከባድ ኃላፊነት ያለበት ሥራ ስለተጣለብን እያንዳንዳችን ኀዘንም ደስታም ይሰማናል ይሆናል ።

ይኸውም ደስ የሚለን ይሠሩልናል ተብለን በምእመናንና በቤ/ክርስቲያን እምነት ተጥለብን በመመረጣችን ነው የሚያሳዝነን ደግሞ በተጣለብን አደራና በተሰጠን ኃላፊነት መጠን ሳንሰራበት ቀርተን ከስና ወቀሳ ሲደርስብን ነው ። ምክንያቱም ይሠሩልናል ተብለው በቤ/ክርስቲያንና በምእመናን ዘንድ እምነት ተጥሎባቸው ሳይሠሩ የቀሩ ሁሉ ታሪክ ሲወቅሳቸውና ሲከሳቸው ይኖራልና ነው ። እኛም ይህን ታሪክ በመገንዘብ የተጣለብንን ኃላፊነት አውቀን ለቤ/ክርስቲያናችን በተገቢው መንገድ ሠርተን ካልተገኘን በታሪክ መወቀስ አይቀርምና በርትተን መሥራት እንዳለብን መንፈሳዊ ግዴታችን ዘወትር ያሳስበናል የሚል ነው ።

ሊ/ማእምራን አበባው ይግዛው በመጨረሻ ንግግራቸው ለውይይታችን መንደርደሪያ ይሆነን ዘንድ በጉባኤው ጽ/ቤት በኩል እስካሁን ስለተከናወኑት ሀበይት ጉዳዮች የሚገልጽ የጉባኤው ዋና ጸሐፊ ሊ/ጉባኤ አበራ በቀለ በአጭሩ ሪፖርት ያሰሙናል ብለዋል ።

ሊ/ጉባኤ አበራ በቀለ ከሰኔ ፲/፲፱፻፸፰ ዓ/ም ማለት ከአንደኛው መደበኛ ስብሰባ እስካሁን ጥቅምት ፲/፲፱፻፸፱ ዓ/ም ድረስ በተለያዩ ቀናት የሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ አባላት እየተሰበሰቡ አንዳንድ የሥራ ፕሮግራሞች ማዘጋጀታቸውንና ጠቃሚ ውሳኔዎችንም ማሳለፋ ጠቁመዋል ። እንዲሁም ከተወሰኑት ተግባራት ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው ።

፩ኛ/ ሀ/በግንቦት ወር ፲፱፻፸፰ ዓ/ም በተካሄደው ስብሰባ በተወሰነው መሠረት ሊ/ኅሩያን መ/ጻድቅ ገ/ሐዮወትና መ/ምርዒት ስብሐት ምስጋናው ወደሲዳሞ ሀ/ስብከት ሄደው በአዋሳ ከተማ የተካሄደውን የሰበካ ጉባኤ ሴሚናር ፕሮግራም በተግባር እንዲገለጽ ያደርጉ ዘንድ ከዚሁ ተልከው በተጠቀሰው ሀገረ ስብከት ከሰኔ ፳/፲፱፻፸፰ ዓ/ም እስከ ሰኔ ፳፱/፲፱፻፸፰ ዓ/ም ድረስ ፕሮግራሙን መርተዋል ፤ የሥራ ክትትልም አድርገዋል ።

፪ኛ/ ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አብያተ ክርስቲያናት የ፲፱፻፸፰ ዓ/ም የጾመ ፍልሰታን ምክንያት በማድረግ የስብከተ ወንጌልና የሰበካ ጉባኤ ሥራ በማቀናጀት ትምህርት ሰጥተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ/ ለሰበካ ጉባኤ አገልግሎት የሚውሉ ቅጾች ለገንዘብና ንብረት መመዝገቢያ የሚያገለግሉ ሞዴሎች ተዘጋጅተዋል ።

፬ኛ በጠቅላላው ጉባኤ በተወሰነው መሠረት ለግምገማና ለቅስቀሳ ሥራ የሚያስፈልጉ የሥምሪት መመሪያና የሰው ኃይል ምደባን በሚመለከት የመጨረሻ ጥናት እንዲደረግበት ለሁለተኛው መደበኛ ጉባኤ ቀርቦአል ። ካለ በኋላ ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ለሥራ ሥምሪት ለየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት በጾመ ፍልሰታ አዲስ አበባ ለተካሄደው የሰበካ ጉባኤ የሥራ ሥም... ላሥራ ክትትልና ለልዩ ልዩ ፕሮግራም የወጣ ገንዘብ በድምሩ ብር 53922.23 (ሃምሳ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሃያ ሦስት ሳንቲም) መሆኑን ዋና ጸሐፊው ገልጸዋል ። ከዚህም በኋላ ጉባኤው ውይይቱን በመቀጠል በ፪ኛ ደረጃ በተያዘው ማለት በቅርቡ ወደ የሀገረ ስብከቱ ስለተላኩት ልዑካን የሥራ ሥምሪት እንዲሁም አሁን ታትመው ስለቀረቡት ቅጾችና ሞዴሎች ለወደፊትም ስለሚታተሙት ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ ካደረገ በኋላ በቀረቡት ረቂቆች ላይ አንዳንድ እርምትና ማሻሻያ ነጥቦችን በመጨመር ቅጾቹ ታትመው በሥራ ላይ እንዲውሉ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ወስኖ አስተላልፎአል ።

ያሳይ ካለፈው በመማር ብርቱ ጥረት ማድረግ እንደሚገባው አማራጭ የሌለው መሆኑን አምኖ ይልቁንም ጉባኤው የዋና ጸሐፊውን ጥረት አድንቆአል ።

በግንቦት ወር ፲፱፻፹፯ ዓ/ም በተደረገው የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ከየሀገረ ስብከቱ የቀረቡትን ሪፖርቶች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥና ጥናታዊ ዘገባዎችን ለማቅረብ እንዲሁም ተሻሽለው የወጡትን የገንዘብና ንብረት ገቢና ወጭ መመዝገቢያ ሞዴሎችን አሠራርና አዲስ የወጡትን ቅጾች ማለት በመላዋ ኢትዮጵያ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ስምና ብዛት ከነትክላቸውና ከነማዕርጋቸው የአገልጋይ ካህናትን የምእመናኑን ብዛትና የገንዘብ አስተዋጽኦን መጠን ለማወቅ የሚያስረዳ ከአጥቢያ ሰበካ ቤ/ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ድረስ በየደረጃው ተሞልቶ የሚቀርብላቸው ቅጾች (ፎርሞች) የመለያ ቁጥር ተሰጥቶአቸው በሥራ ላይ እንዲውሉ የቀረበውን ሀሳብ በመቀበል ቁጥር ፩ ከቅጽ (ሀ እስከ ሠ) ለአጥቢያ ፥ ለወረዳ ፥ ለአውራጃ ፥ ለሀገረ ስብከት ፥ ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲሆን ጉባኤው ወስኖአል ።



ሊቀ ማእምራን አጠቃላይ የሰበካ መ/ አስተዳደርን በሊቀ መንበርነት ሲመሩ

ጉባኤው በዋና ጸሐፊው የቀረበው ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ በአራት ወራት ውስጥ የተከናወኑት ሥራዎች ጥሩ ውጤት ስለተገኘባቸው(ስለታየባቸው) ለወደፊት የበለጠ የሥራ ክንውን ለማየት እንደሚቻል ሙሉ እምነት ጥሎበታል ። ስለሆነም ጽ/ቤቱ በበለጠ ተጠናክሮ ከዚህ የበለጠ የሥራ ውጤት እንዲ

እንዲሁም በየሀገረ ስብከቱ የሚዘምቱ ልዑካን ለመጀመሪያ ጊዜ በእያንዳንዱ አውራጃ ርእሰ ከተማ ላይ የየወረዳዎቹ ሊቃነ ካህናትና የሰበካ ጉባኤያት ተጠሪዎች በሚገኙበት ቦታ ሰሚናር ቢሰጥ ውጤት ሊኖረ... ...ንደሚችል ጉባኤው በመገመት ለዚሁ ተልእኮም ከመንበረ ፓትርያርክ አጠ



ቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጥናታዊ ዘገባ መሠረት ሁለት ሁለት ልዑካን ከመመደቡም በላይ ለልዑካኑም በመንበረ ፓትርያርክ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ የሁለት ቀን ሴሚናር ሰጥቶ ዘመቻው ከታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ጀምሮ እንዲቀጥል አድርጎአል ።

በስምሪት አንድ የተሰጡት መመሪያዎች በሥራ መተርጎማቸውን ለማረጋገጥ የሁለተኛው የሥራ ስምሪት ግምገማ ከሦስት ወር በኋላ እንዲካሄድ ጉባኤው ለጽ/ቤቱ መመሪያ ሰጥቶ የሚቀጥለውን ስብሰባ ለጥቅምት ፺ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ከቀኑ በ፱ ሰዓት እንዲሆን ተስማምቶ የዕለቱ ስብሰባ በጸሎት ከተዘጋ በኋላ የጉባኤው አባላት በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የሰበካ መንፈሳዊ አጠቃላይ ሊ/መንበር አማካይነት ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቀርበው ቡራኬና መመሪያ ተቀብለዋል ።

ጥቅምት ፺ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ጉባኤው እንደ ተለመደው በዋና ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ተገኝቶ ከአንድ እስከ ስምንት ድረስ አጀንዳ በማውጣት በአጀንዳዎቹም ላይ አንድ በአንድ እየተነጋገረ ውሳኔ በመስጠትም እያሳለፈ በተግባር ገልጾአል ።

ጉባኤው ከአጥቢያ ቤ/ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ድረስ በየደረጃው እንዲሠራባቸው ተዘጋጅተው የቀረቡትን ቅጾችና ፲፮ ልዩ ልዩ ዓይነት የገንዘብ ገቢና ወጭ መመዝገቢያ ካርኒዎችና የንብረት ገቢና ወጭ ሞዴሎች ታትመው በሥራ ላይ እንዲውሉ በዝርዝር በቀረበው መሠረት በፊርማ አጽድቆአቸዋል ።

በመጨረሻም ጉባኤው አጠቃላይ በሆኑ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የሀሳብ ልውውጥ ካደረገና በሰፊው ከተወያየ በኋላ ስለውሳኔዎቹ ተግባራዊነት ለጽሕፈት ቤቱ አንዳንድ መመሪያዎችን ሰጥቶ የሁለተኛውን መደበኛ ስብሰባ ልክ ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ላይ በጸሎት ፈጽሞአል ።

በዚሁ ዕለት ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና የጠ/ቤተ ክህነት የየመምሪያው ኃላፊዎች በተገኙበት በዚሁ ባሥራ ለሰነበተው ጉባኤ በመንበረ ፓትርያርኩ አዳራሽ የራት ግብዣ ከተደረገለት በኋላ ጉባኤው የተጣለበትን አደራ ለመወጣት ይችል ዘንድ ቅዱስነታቸው ሰሞኑን ሲያከናውኑት የሰነበተውን አመስግነው አባታዊ ምክርና መመሪያ ሰጥተው አሰናብተዋል ።

# በየሀገረ ስብከቱ ለሚዘምቱ ልዑካን የሦስት ቀን ሰሚናር ተሰጣቸው

አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ሊቀ መንበር ሰብሳቢነት ከጥቅምት ... እና ጥቅምት ፺ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ባደረገው ታሪካዊና ጥናታዊ ጉባዔ አማካይነት በግንቦት ወር ፲፱፻፹፮ ዓ/ም ከየሀገረ ስብከቱ የቀረቡትን ሪፖርቶች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ና ጥናታዊ ዘገባዎችን አጥንቶ ለማቅረብ ፥ እንዲሁም ተሻሽለው የወጡትን ቅጾች በመላዋ ኢትዮጵያ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ስምና ብዛት ከነ ማዕረጋቸው የአገልጋይ ካህናትና የምእመናኑን ብዛትና የገንዘብ አስተዋጽኦን መጠን ለማወቅ የሚያስረዳ ከአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መ/ጉባዔ ድረስ በየደረጃቸው ተሞልተው የሚቀርቡ ቅጾች የመለያ ቁጥር ተሰጥቶአቸው በሥራ ላይ እንዲውሉ የቀረበውን ሀሳብ በመቀ... ቁጥር ፩ ቅጽ /ሀ/ እስከ /ሠ/ ለአጥቢያ ለወረዳ ለአውራጃ ለሀገረ ስብከት ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ...ካ መ/ጉባዔ እንዲሆን ጉባኤው መወሰኑ ይታወሳል ።

በዚሁ መሠረት ለዚሁ ስምሪት የተመረጡት ልዑካን ከኅዳር ፲፱ እስከ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ድረስ በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤ/ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀ መንበር ሰብሳቢ ከ፴ ለማያንሱ መልእክተኞች በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ሰሚናር ተሰጥቶአቸዋል ።


በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ከመንበረ በትረ ክህነታቸው እንደ ተገኙ ጉባዔው በጸሎተ ወንጌል ተከፍቶአል ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የወንጌሉን ማብራሪያና የመልእክት ኖትንም መመሪያ ሰጥተዋል የቅዱስነታቸው መመሪያ ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጿል ።

ሥራው አንድ ጊዜ ተሠርቶ ውጤት ሊኖረው አይችልም በየሰዓቱ በየወቅቱ እየተመላለሱ ካልነበሩት ካላጠናከሩት ውጤት ሊኖረው አይችልም ።



www.ethiopianorthodox.org



ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የልዑካኑን ሴሚናር በንግግር ሲከፍቱ

ለምሳሌ ገበሬ እርሶ አለስልሶ ዘርቶ ብቻ ዝም ቢል አረሙ ቁጥቋጦው ይውጠውና ያጠፋዋል ። ነገር ግን ገበሬው እህሉን ከዘራበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሰለች አረሙን አርሞ ኰትኩቶ እንስሳት አራዊት እንዳያጠፉበት ቢጠብቀው ከምድሩ በረከትና ረድኤት ያገኛል ።

እኛም ይህ የቤ/ክርስቲያኖችን አለኝታ የሆነው ሰበካ ጉባዔ አንድ ጊዜ ብቻ ሠርተናል ብለን ዝም እንዳንል በየጊዜው ተግተን እንድንሠራ ሰበካ ጉባዔውን ስብከተወንጌልን በሚገባ ተግተን መሥራት ስላለብን ይህንኑ ለመወያየት ነውና የተሰበሰብነው መበርታት ይገባናል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እባቡም ጊንጡም አይጉዳችሁም ብሎአል በእርግጥ በእርሱ ያመነ ሥራውም በእምነት ያከናወነ ምንም አይጎዳውም ምንም አይነካውም ስለዚህ በቃለ አዋዲው መሠረት ተግቶ መሥራት እንደሚገባን በሥራችንም ምንም እንከን እንደማይገጥመን ቃሉ ስለሚያበረታታን በተሰጠን አደራ የሚፈለግብንን ተልእኮ መወጣት አለብን ። —

እረኛ በጎቹን በአጠቃላይ መንጎቹን በርትቶ ጠንክሮ ካልጠበቃቸው ነጣቂ አውሬ ያጠፋቸዋል። እኛም ምእመናኖቻችን በተገቢ መንገድ ልንጠብቃቸው ይገባናል ።

አሁን የምትሄዱበት ጉዳይ መነሻው ሰበካ ጉባኤ ቢሆንም ልማትም ስብከተ ወንጌልንም ለማጠናከር ነው ። ዓላማችን ተልእኮአችን ይህ ነውና የቤ/ክርስቲያናችን ዕድገትና ልዕልና ለማየት የምንችለው እነዚህን አጠናክረን የተገኘን እንደሆነ ነው

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባቱን አባት ሆይ ይህን ለሐዋርያት ስለገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ ። እንዳለው ሁሉ እነዚህ አደራ የተጣለባቸው ተመራጮችም ለሰበካ ጉባዔ ጠቃሚ የሆኑ ሞዴሎችን እንዲያዘጋጁበ መታደላቸው ሊመሰገኑ የሚገባቸው ነው በመሆኑም ይህን ጥበብ ለሐዋርያት ስለ ገለጥህላቸው እናመሰግንሃለን ብለን እያንዳንዳችን ፈጣሪያችንን ልናመሰግን ይገባናል ።

ሁለት መቶ ሺህ ካህናት ሃያ ሺህ አብያተ ክርስቲያናት አሉን እንላለን ምናልባት ግን ያውቃል



ይበዛሉ ወይም ያንሳሉ ነገር ግን በትክክል ለማወቅ እንዲቻል አብያተ ክርስቲያናት ምን ያህሉ እንደ ሆኑ መቼ እንደ ተተከሉ ማን እንደ ተከላቸው በማን ዘመን እንደ ተተከሉ የሚመዘገብበት ቅጽ ተዘጋጅቶ ስለቀረበና ይህንኑም በብዙ ድካምና ጥበብ በተመላበት ሠርተው ያቀረቡትን ደግመን ደጋግመን ልናመሰግናቸው ይገባናል ።

እንግዲህ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ሁለት ሁለት አድርጎ ለስብከተ ወንጌል ሥራ እንደ ላካቸው ሁሉ እናንተም ቤ/ ክርስቲያን ጠርታ ስትልካችሁ መልካም እድል ስለሆነ ለዚሁ ለተቀደሰ ተግባር ትበረቱ ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናንተ ጋር ይሁን በማለት በረከታዊ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል ።

ከዚህ በፊት ግን ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀ መንበር ጉባኤውን በንግግር ከፍተዋል ። ይኸውም «ዛሬ በዚህ ሥፍራ ቅዱስነታቸው ይህ የመልእክተኞች ስምሪት ሴሚናር በጸሎት እንዲከፍቱልን የተቀደሰ ፈቃዳቸው ሆኖ በመካከላችን ስለተገኙልን ፈጣሪያችንን ከልብ እናመሰግነዋለን ። ካሉ በኋላ የሰሚናሩ ዓላማና ተግባር አንድ በአንድ ተንትነው ገለጸ አድርገዋል ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀ መንበር ካደረጉት ንግግር ውስጥ «ይህ አሁን ስለ ሰበካ ጉባኤ ሴሚናር መጠናከር የምናደርገው ከፍተኛ ጥረት እንደዛፍ ወይም እንደ ተክል ተካይ አድርገን ልንመለከተው ይገባናል ። አንድ ተክል ተካይ ዛሬ ተክዬ ዛሬ ፍሬ ለማግኘት እንድችል ነው አይልም ። የሚፈልገው ፍሬ ለማግኘት ብዙ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ያውቃል ነገር ግን ተስፋ ቆርጦ ተክሉን ከመትከል አይቆጠብም ።

እኛም ዛሬ ተክል እንትከል ነገ የሚተኩት ደግሞ ውኃ ያጠጡት ተክሉ አድጎ ለምልሞ ያብባል ። ከዚያ በኋላ የሚነሡት ደግሞ መልካም ፍሬ እንዲያፈራ ያደርጉታል ። ለመልካም ተግባር ያውሉታል በመሆኑም ይህ የተጣለብን ታሪካዊ ተግባር በቀና መንፈስ ተነሥተን መሥራት አለብን ።

ስለዚህ ቅዱስነትዎ ለልዑካኑ ጠንከር ያለ መመሪያ እንዲሰጡልን በቤ/ ክርስቲያን ስም ከፍ ባለ ትሕትና እጠይቃለሁ ብለዋል ።

ከዚህ በኋላ ሰሚናሩ እስከ ሦስት ቀን ቀጥሎ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ልክ ፲፩ ሰዓት ሲሆን በጸሎት ተፈጽሞአል ።

# የጫጋል ቀራንዮ መ/ዓለም ቤ/ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት ተከበረ ፤

በሰላሌ አውራጃ በደብረ ጽጌ ወረዳ በደብረ ሊባኖስ አካባቢ የሚገኘው የጫጋል ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ኅዳር ፲ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ቅዳሴ ቤቱ ተከብሮ ውሎአል ቀደም ሲል ይህ ቤ/ክርስቲያን ያሠሩት ልዑል ራስ ካሣ ዳርጌ ሲሆኑ በዘመን ብዛት አርጅቶ ተሰንጣጥቆና ፈርሶ ስለ ነበር የአካባቢው ምእመናንና በአዲስ አበባ የሚገኙት የቀበሌው ተወላጆች በመተባበር ፤

፩ኛ/ የቤ/ክርስቲያኑ ዙሪያ የተጣፈነና በጣም ጠባብ ስለነበረ ዙሪያው እንደ ልብ ለመዘዋወር በሚያስችል ሁኔታ ተሠርቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ፤

፪ኛ/ የዕቃ ቤት ስላልነበረውና የቤ/ክርስቲያኑ ንብረት የሆኑትን የክቡሩ ንዋየ ቅዱሳት ሁሉ በልዩ ልዩ ጉድለት በመበላሸታቸውና በመጥፋታቸው ምክንያት በጠቅላላ ቤተ ክርስቲያኑ በአገልግሎት አሰጣጡም ሆነ በሕልውናው ጉስቁልና ስለደረሰበት ባማረ ሁኔታ ተሠርቶ ተገቢ መንፈሳዊ አገግሎቱን እንዲሰጥ ለማድረግ ነው ።

ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ሥርዓተ ዋዜማው ከተከናወነ በኋላ ቤ/ክርስቲያኑ ተባርኮ ታቦቱ ከነበረበት መቃኞ ወደ ጥንተ መንበሩ ገብቶአል ።


ከዚያም ሊቃውንቱ ስብሐተ እግዚአብሔሩን ሲሊቱን ሙሉ ሲያበረክቱ አድረዋል ሥርዓተ ቅዳሴው ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ተጀምሮ እስከ ሁለት ሰዓት ከቀኑ ተከናውኖአል በቅዳሴው ስነ ሥርዓት ላይም ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ የኢትዮጵያ ገዳማት ኃላፊ ጸባቴ አርአያ ሥላሴ አጽብሐ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪና የገዳሙ አበው መነኮሳት እንዲሁም በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ምእመናን ተገኝተዋል ።

ከቅዳሴው ፍጻሜ በኋላ ታቦቱ ወደ ጸበሉ አምርቶ ከስፍራው እንደደረሰ ሥርዓተ ጸሎት ተከናውኖአል ከዚያም ተመልሶ ሥርዓተ ዑደቱ ተፈጽሞ ከተመደበለት ሥፍራ እንደቆመ መዘምራት ለ፲፭ ደቂቃ ያህል ያሬዳዊ መዝሙር በማሰማት አሸብሽበዋል ።

ከዚያም ጸባቴ አርአያ ሥላሴ አጽብሐ ስለ ገዳሙ ታሪክና ስለ አሠራሩ በሰፊው ተንትነው ገለጸ አድርገዋል ። ከዚህም ቀጥሎ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ የኢትዮጵያ ገዳማት ኃላፊ ዕለቱ በዓሉን በሚመለከት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ሰፊ ትምህርት ሰጥተዋል ቀደም ሲልግን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ሰባክያን ትምህርተ ወንጌል ሲሰጡ ቆይተዋል እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያኑ



www.ethiopianorthodox.org



የጫጋል መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ይህ ነው ።

ሥራና እድሳት ኮሚቴ አባሎች አንዱ ኮሚቴውን በመወከል ስፋ ያለሪፖርት በንባብ አስምተዋል ።

ከሪፖርቱ ውስጥ ፩ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ይህንኑ ቤ/ክርስቲያን እንዲጎበኙልን ባሳሰብነው መሠረት ታኅሣሥ ፳፩ ፲፱፻፸፱ ዓ/ም መጥተው ሲጎበኙ የእናጺ ነትና የግምበኝነት ሙያ ያለው አንድ ሠራተኛ እልክላችኋለሁ ብለው በሰጡን የመንፈሳዊ አባት ተስፋ መሠረት አቶ ጌታቸው ክብረትን ልከው እነሆ ግምቱ እስከ መቶ ሺህ የሚደርስ የገንዘብ ወጭ የሚጠይቀውን ሂሳብ ሸፍነው ይህን የመሰለ ቤ/ክርስቲያን ሠርተው ስላስረከቡን በእስራው ኮሚቴ ስም ለቅዱስነታቸው ከፍ ያለ ምስጋናየን በትሕትና አቀርባለሁ ።

፪ኛ/ አባታችን ጸባቴ አርአያ ሥላሴ አጽብሐ ብዙ ምእመናንን በማስተባበር ከፍተኛ የገንዘብ ርዳታ ያስገኙልን ከመሆናቸውም በላይ በትርብ ሆነው ሥራውን በመከታተልና አሠሪ ኮሚቴውን በማበረታታት ያሳዩት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ምን ጊዜም የማይረሳ ተዋሚ ታሪክ ነው ።

፫ኛ/ አቶ ዘገየ መስተሉ ከብዙ ማተሪያል ርዳታ ሌላ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ ብር)

፬ኛ/ ወ/ሮ ማሚቴ በዛ ብር ፩ሺ (አንድ ሺ

፭ኛ/ አቶ ተድላ ገ/ሥላሴ ከልዩ ልዩ ስጦታ ሌላ ፩ሺ፭፻ (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር)

፮ኛ የቅ/ገብርኤል የወንድማማች ማኅበርተኞች በአቶ ወልደ ገብረ ሕይወት አማካይነት ብር ፩ሺህ (አንድ ሺህ)

፯ኛ/ አቶ አያሌው ወ/ማርያም ከብዙ ትሩፋታቸው ሌላ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ።

፰ኛ/ አቶ አበበ ክብረት አቶ ነጋሽ ላቀው ሻምበል ከንፈ ዓለማየሁ እያንዳንዳቸው ብር ፭፻ ብር(አምስት መቶ ብር)

፱ኛ/ አቶ ወርቅነህ አይቸግረው ብር ፬፻ (አራት መቶ ብር)

፲ኛ/ ከቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድና በሰበካ ጉባኤው መተባበር ለአንድ ቀን ብቻ ርዳታ ጠይቀን ብር ፫፻-፶ (ሦስት መቶ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ።

፲፩ኛ/ አቶ ጌታቸው ክብረት አሁንም ብዙ ወጭ ከሚጠይቀን የእናጢነትና የግምበኝነት ሥራ ሌላ አንድ ሙሉ መኪና አሸዋና በገንዘብም በኩል ከብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ያላነሰ እንዲሁ ም ከጀዳ አስልከው አንድ የወርቅ መንናጸፊያ ለቤተ መቅደሱ መገልገያ ሰጥተዋል ።

፲፪ኛ/ አቶ መልአኩ ወልደየስ ለዚሁ ቤ/ ርስቲያን ፍጻሜ መብቃት አንደኛ ስለሆኑ ምእመናን የኒሁ ትጉህ ክርስቲያን የተቀደሰ አስተዋጽኦን እንድትገነዘቡልን እንወዳለን ።



፲፫ኛ/ የሰበካው ጉባኤ ሊ/መንበር መምሬ ደመቀም ሌት ተቀን ያለዕረፍት በየአውራጃውና ወረዳው ከበጎ አድራጊዎች ገንዘብ እየሰበሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

፲፬ኛ/ አቶ ቢክተሪ ጆርጅ ከፍተኛ ወጭ ያስከትል የነበረውን የቤ/ክርስቲያኑ መስኮቶችና የብረት መዝጊያ ያለምንም ክፍያ በነፃ ጉልበታቸው የሠሩና በየጊዜውም ከቤ/ክርስቲያኑ ድረስ እየተገኙ ጉባኤውን በመቀየስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ናቸው ።

፲፭ኛ/ አቶ ማሞ አጥሬ አቶ ማስረሻ አበበ አቶ ኃይሉ ገብረ ጻድቅ እያንዳንዳቸው ብር ፩፻ ብር (አንድ መቶ ብር) ።

፲፮ኛ ወ/ሮ አልማዝ ታዬ ብር ፩፻፶ አንድ መቶ ሃምሳ ብር ወ/ሮ ብርቅነሽ ብር ፪፻፲ (ሁለት መቶ አሥር ብር) ረድተዋል እንዲሁም አቶ እየሶ ደምስ ሥራው እስከ ተፈጸመ ድረስ ተባብረዋል ።

፲፯ኛ/ የአካባቢው ምእመናንና ነዋሪው ሕዝብም ጉልበቱንና ገንዘቡን በማስተባበር ለክብረ በዓሉ ግብዣ በማዘጋጀትና ዕንግዳን በመቀበል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል የሚል ይገኝበታል።

ከዚህ ንግግር ፍጻሜ በኋላ ጃንጥላ ዞር በርክት ያለ ገንዘብ ተገኝቶአል ከዚህም አያይዘው ብፁዕነታቸው ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።

በገዳሙ ቅጥር ውስጥ ፩፻ (አንድ መቶ) ችግረኞች የሚይዝ በጸባቴ አርአያ ሥላሴ አጽብሐ አማካይነት የተሠራ ቤት ይገኛል ። ከዚሁ ቤተ ክርስቲያን ጋር ባለአንድ ፎቅ ቤትና የእመቤታችን ጽላት ያለበት ቤ/ክርስቲያን ተሠርቶአል ። የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤ/ክርስቲያን ተሠርቶ እስካለቀ ድረስም ታቦቱ በዚሁ ቤተ ክርስቲያን እንደቆየ ታውቆአል እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በትክክለኛ አመለካከት ሕንፃው ስንገምተው ከመቶ ሃምሳ ሺህ ብር ያላነሰ ወጭ እንደሚጨርስ አያጠራጥርም የጫጋል መድኃኔ ዓለም ቤ/ክርስቲያን ተወዳዳሪ የሌለው ነው ። እጅግ በጣም ሊመሰገኑና መልካም አርአያና ምሳሌም ሊሆኑ የሚገባቸው ጸባቴ አርአያ ሥላሴና የአሠሪ ኮሚቴው እንዲሁም የአካባቢው ምእመናን ናቸው ።

እንደነ አቶ ጌታቸው ክብረት ያሉ ለሃይማኖታቸው ለሃገራቸው የሚቀረቆሩ የሚሠሩና የሚያሠሩ ባንዳንድ ኑፋቄ ገጠር ቢገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተሕዋዶ ቤ/ክርስቲያን ከዳር እስከ ዳር ተስፋፍቶ ነበር ለማለት ይቻላል ።

# በአታ ለማርያም ፤

እመቤታችን ድንግል ማርያም የብጽዓት ልጅ ናት አባትና እናቷ በተወለደች በሦስት ዓመቷ ወስደው ከቤተ መቅደስ አግብተዋታል ። ስለዚህ ያቺ ቀን በዓታ ተብላ ተጠርታለች ይኸውም እመቤታችን ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት ዕለት ማለት ነው ።

አባቷ ኢያቄምና እናቷ ሐና በሕግ ተጋብተው ሲኖሩ ለዓይናቸው ማረፊያ ለልባቸው ተስፋ የሚሆን ልጅ ባለ መውለዳቸው (በማጣታቸው) ጽኑዕ ኀዘን ተሰማቸው ይልቁንም በዘመናቸው የነበረው ሊቀ ካህናት እናንተማ እንኳ ብዙኑ ወተባዝ ኑወምልዕዋ ለምድር ተብሎ ለአዳም ስለተነገረው ተስፋ የቀረባችሁ ርጉማን ብትሆኑ አይደለምን እያለ መባ አቸውን በመመለሱ ምርር ያለ ልቅሶ አልቅሰዋል ። ከዚህ የተነሣ ሐና ፍጥረታቱን ሁሉ በባህርያቸው እንዲራቡና እጸዋትን በባህርያቸው እንዲያብቡ እንዲያፈሩ የምታደርግ ከሆ የኔ ተፈጥሮ ከምን ይሆን ብላ ዋይታዋን (ልመናዋን) ወደ እግዚአብሔር በማሰማት ከባሏ ጋር በአንድነት ሁነው ወንድ ልጅ ብንወልድ ወጥቶ ወርዶ አርሶ ቆፍሮ ይርዳን አንልም ሴትም ብትሆን ለቤተ እግዚአብሔር መሶበ ወርቅ ፍታ መጋረጃ ፈትላ ትኖራለች ሲሉ ቸርነቱና ይቅርባይነቱየ ባህርዩ ለሆነ አምላክ ቃል ገብተው ስውነታቸውን በጾም በጸሎት ወስነው መኖርን መርጠዋል ። በጾም በተግታ ሰውነትና በጸሎት በታረመ አንደበት ክሳደ ልቡናንና ዓይነ ህሊናን አቅንቶ ለእግዚአብሔር ልመናን መግለጽ የንጹሐን አበው መንፈሳዊ መመሪያ ለመሆኑ ሐና እመ ሣሙኤልን ማውሣት በቂ ምስክር ነው ።

በሴሎ መሥዋዕቱን ከበሉና ከጠጡ በኋላም ሐና ተነሣች ካህኑ ኤሊ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በመንበሩ ላይ ተቀምጦ ነበር እርሷም በልብዋ ታዝን ነበር ። በእግዚአብሔር ፊት ጸለየች ጽኑ ለቅሶም አለቀሰች እርሷም አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ የባሪያህን መዋረድ ተመልክተህ ብታስበኝ እኔንም ባትረሣ ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሠጥ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም ብላ ስእለት ተሣለች ጸሎትዋንም ለእግዚአብሔር ባቀረበች ጊዜ ዔሊ አፉዋን ይመለከት ነበር ። ሐናም በልብዋ ትናገር ነበር ድምጿም ሳይሰማ ከንፈሯን ታንቀሳቅስ ነበር ። ዔሊም እንደ ሰከረች ቆጠራት ዔሊም ስካርሽ እስከ መቼ



www.ethiopianorthodox.org

ነው? የወይን ጠጅሽንም ከአንቺ አርቂው አላት ሐናም ጌታ ሆይ አይደለም እኔስ ልቧ ያዘነባት ሴት ነኝ ጠጅና ሌላ የሚያሠክር ነገር አልጠጣሁም ።

ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ነፍሴን ጣልሁ ኃዘኔና ጭንቀቴ ስለበዛ እስከ አሁን ድረስ ተናግሬ አለሁና ባርያህን እንደምናምንቴ ሴት አትቁጠረኝ ብላ መለሠችለት ዔሊም በደኅና ሂጂ የእስራኤልም አምላክ የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ ብሎ መለሰላት እርሷም ባሪያህ አይንህ ፊት ሞገስ ላግኝ ብላው ወደቤቷ ተመለሰች ከዚህ በኋላ የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሣ ቸር አምላክ ስእለቷን ተቀብሎ ጸሎቷን ሰምቶ ወንድ ልጅ ሰጣት ኃዘኗን ወደ ደስታ ልቅሶዋንም ወደ ሣቅ መልሶላታል እርስዋም በእግዚአብሔር ቸርነት ወንድ ልጅ ጸንሳ በመውለዷ ደስ ብሏት ጸሎቷን ስእለቷን እግዚአብሔር ሰማኝ ስትል ስሙንም ሳሙኤል ብላ ዋለች በተወለደም በሦስት ዓመቱ በገባችው ቃል መሠረት ያጫወተኝ ይርዳኝ ሳትል ወስዳ ለቤተ እግዚአብሔር ሰጥተዋለች እርሱም በእግዚአብሔር ተመርቶ የእግዚአብሔር ነብይ ተብሎ ኃላፊያትን እየተናገረ መጻእያትን እየተነበየ እግዚአብሔርን ሲያገለግልና እስራኤልን ሲመክር ሲገስጽ /ሲያስተምር/ ኑሮአል ። (ቀዳማዊ ሣሙኤል ምዕራፍ ፩ ከቁጥር ፩ እስከ መጨረሻው) ።

ኢያቄምና ሐናም እምነታቸው በእግዚአብሔር አድርገው በጾምና በጸሎት ተወስነው ልጅ እንዲሰጣቸው ስለለመኑት ድንግል ማርያምን ለመውለድ ቻሉ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር በስተቀር ሰጪና ነሺ የሌለ መሆኑን በማመን ጸንተው ሌትና ቀን ጸሎታቸውን ሳያቋርጡ በመማጸናቸው በብስራተ መልአክ በፈቃደ አምላክ ጸንሰው እንደ ወለዱአት ታሪክ ይመሰክራል ፤ በመግቢያው እንደተገለጸው ሁሉ ሦስት ዓመት ሲሆናት ሐና ኢያቄምን በገባነው ቃል ኪዳን መሠረት ይህች ብላቴና/ይህች ህጻን/ አፏ እህል ሳይለምድ ሆዷ ዘመድ ሳይወድ ወልደን አንሠጥምን? የሰጠ ቢነሣ የለበት ወቀሣ እንዲሉ አንዳችብትሆንብን ከልጃችንም ከእግዚአብሔር ሣንሆን እንቀር የለምን ብላ ነገረችው ። ኢያቄምም ፍቅርሽ ይለቅልሽ ብየ ነው እንጂ ፈቃደኛ ነኝ ብሏታል ። ከዚህ በኋላ በዘመናቸው የነበረው ሊቀ ካህናት ለዘካርያስ ወስደው ሰጥተዋታል ። ዘካርያስም ሕዝቡን ሰብስቦ የምግቧን ነገር ይያዝልኝ እያለ ሲያወያይ የናት የአባቷን ልመና የሰማ እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ መኖርዋ ፈቃዱ ስለሆነ መልአኩ ፋኑኤል ልኮ ኅብስት ሰማያዊ መግቦአት ጽዋዕ ሰማያዊ አጠጥቷት ተመልሶ አርጓል ፤ ሊቀ ካህናቱም የምግቧ ነገር ከተያዘ ከሰው ጋራ ምን አጋፋት ብሎ ታህሣሥ ፫ ቀን ፭ሺ፬፻፹፰ ዓመተ ዓለም ከቤበ መቅደስ አግብቶ አኑሮአታል ። ሊቁም መላእክት ምግብሽን እያመጡልሽ አስራ ሁለት ዓመት ሙሉ እንደዚህ ኖርሽ ብሏል ። ታዲያ በየ ዓመቱ ታህሣሥ ፫ ቀን ጧፍ ይዘው ዕጣን ቋጥረው ግብር ሠፍረው በድንግል ማርያም ስም ወደ ታኑ ፀውት አብያተ ክርስቲያናት ከከተማም ሆነ ከገጠር የተለያየ አገልግሎትን ለማበርከት የሚጐርፉ ምእመናን ስፍር ቁጥር የላቸውም ከዚህም ጋር በጾም በጸሎት ተወስነው ቃል ኪዳኗን ተማጽነው በአማላጅነቷ ጸንተው ስሜን የሚጠሩና የሚያስጠሩ ምእመናን በየአብያተ ክርስቲያናቱ እንዳሉ ሥራቸው ምስክር ነው ። ስለዚህ ከላይ እንደተነገረው ይኸንኑ እመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበ ትን በአል በየወሩና በየዓመቱ ለማክበር የሚችል የተቀደሰ ልቡና ይስጠን ዘንድ የዕለታትና የሰማያት ፈጣሪ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን ። አሜን

ቀኝ ጌታ ያሬድ ሞላ ሰባኬ ወንጌል



# ሳሙኤል ዘዋልድባ

ጻድቁ አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ ኢትዮጵያዊ ናቸው ። የተወለዱበትም ቦታ ትግራይ ክፍለ ሀገር አክሱም አውራጃ ነው ።

አባታቸውም የአክሱም ደብረ ጽዮን ገበዝ ከነበረና የጌዴዎን ወገን የሆነ እስጢፋኖስ የተባለ ሲሆን እናታቸውም ዓመተ ማርያም ትባላለች ። አቡነ ሳሙኤል ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚሁ በተወለዱበት ቦታ በአክሱም ገዳም ፊደል ቆጥረው መዝሙረ ዳዊትንም ደግመው በጠቅላላ ለመዓርገ ዲቁና የሚያበቃቸውን መንፈሳዊ ትምህርት ተምረው ገና በሕጻንነታቸው ሳሉ አባታቸውና እናታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል እሳቸውም የአባታቸውና የእናታቸው በሞት መለየት ካዩ በኋላ ይህ ዓለም ለአባቴና ለእናቴ ካልሆነ ለእኔስ ምን ይረባኛል ምንስ ይጠቅመኛል ብለው ስለ ዓለም ሁኔታ በሐሳብ ሲያወጡና ሲያወርዱ ከቆዩ በኋላ ወድያውኑ ተነሥተው ከአክሱም በስተ ምዕራብ ወደሚገኘው አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የቆረቆሩትና ደብረ በንኮል በመባል ወደ ታወቀው ገዳም መንነው ሄዱ ደብረ በንኮል ማለትም ሙራደ ቃል ማለት ነው ።

አቡነ ሳሙኤል ከገዳሙ እንደ ገቡ ለገዳሙ የሚያስፈልገውን ሥራ በመሥራትና ማኅበሩ ያዘዛቸውን ትእዛዝ እየፈጸሙ በደብረ በንኮል ገዳም የሚገኙትን አበው መነኮሳትን ደስ አሰኟቸው ።

በተለይ ገዳሙን የቆረቆሩት አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የአቡነ ሳሙኤልን መንፈሳዊ ሥራንና የሚፈጽሟቸውን ልዩ ልዩ የሆኑትን ሥራዎች በማየት በአድናቆት ይመለከቷቸው ነበር የአቡነ ሳሙኤል ደግነትና ብቃት ከዕለት ወደ ዕለት እየጎላና እየተገለጠ ሲሄድ በማህበሩ ዘንድ እየታወቀ ስለሄደ ብቃታቸው በመመልከትና ከእሳቸው የሚያገሡ መሆናቸውን በመገንዘብ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ አልባሰ ምንኩስናን አለበሷቸው አስኬማ ሥላስክትንም አስታጠቋቸው ።

አቡነ ሳሙኤልም ከመነኮሱ በኋላ «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ ማንም ዓለምን ቢወድ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ»ሲል ወንጌላዊው ዮሐንስ በ፩ኛ መልእክቱ ፪ ፣ ፲፭ የተናገረው በተግባር ለመተርጎም ፊት በርድእና ይሠሩት ከነበረው መንፈሳዊ ተግባር እጥፍ ድርብ በመሥራት ሰውነታቸውን በገድል አደከሟት

ጻድቁ አቡነ ሳሙኤል የተለያዩ ምግባር ትሩፋትን በመሥራት ሰውነታቸውን አደከሟት ቢባሉም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የበረቱ ስለ ነበሩ በመንፈሳዊ ኃይልም እየበረቱ በመሄዳቸው አስደናቂና አስገራሚ የሆነውን ተአምራት ያሳዩ ጀመር በተለይ እንደ እነ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ሐኪዊን እሳት ደርሰው ስለ ነበሩ እሳቱ ይፈጀኛል ብለው ሳይፈሩ ከእሳት ላይ የተጣደውን የማህበሩን ንፍሮ በእጃቸው ሲያማስሉት ፈጽሞ አይፈጃቸውም ነበር ይላል ገድላቸው ።

እንዲያውም ታሪክ እንደሚናገርላቸው አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የአቡነ ሳሙኤል ሥራ ተመልክተው አባ ሳሙኤል ንፍሮውን በእጁ ሲያማስለው እኔስ በእጄ ባማስለው ምን አለ እኔ ከእሱ እበልጣለሁ እንጂ አንሳለሁን? ብለው ተዳፍረው እጃቸው ከተጣደው ድስት አስገብተው ንፍሮን ለማማስል ቢሞክሩ ፍላቱ ፈጃቸውና«እስመ ዓዲ ኢአረገ ኅበ መዓርገ ዚአከ» አንተ ከደረስክበት ደረጃ አልደረስኩም ተብሎ የተጻፈው ለካ ከዚህ የተነሣ ነው እኔ እንዲህ አልመሰለኝም በማለት በሠሩት ድፍረት ተጸጽተው እጃቸውን ሰብስበው ተቀመጡ ይባላል ።

ከዚህ በኋላ አቡነ ሳሙኤል ከደብረ በንኮል ወጥተው ከአናብስትና ከአናምርት በስተቀር የሰው ድምጽ ወደ ማይሰማበት ጫካና ዛሬ ደብረ ዓባይ ወደ ተባለው ገዳም ገቡ ከዚያውም ገብተው በጾምና በጸሎት ተወስነው ብዙ ዘመናት ካሳለፉ በኋላ ወደ ዋልድባ ገዳም ሄዱ ዋልድባ ምንም እንኳን ከአቡነ ሳሙኤል በፊት ቀደም ሲል የተቆረቆረና ብዙ ዘመናት የነበረ ታላቅ ገዳም ቢሆንም ጠፍቶ ስለነበር እንደ ገና አቡነ ሳሙኤል መነኮሳትን ሰባስበው ገዳሙን አቅንተው አቋቋሙት ።

አቡነ ሳሙኤል ያሳዩትና ይሠሩት የነበረው ተአምራት ይህ ብቻ አልነበረም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እጅግ ከመውደዳቸው የተነሣ ቅዳሴውን ሳያደርሱ በምንም አይነት እህል አይቀምሱም ነበር ጻድቁ አቡነ ሳሙኤል ይህንን የእመቤታችንን ቅዳሴ እየደገሙ በሚሄዱበት ወቅት ከመሬት አንድ ክንድ መጥቀው ይሄዱ እንደነበር ገድላቸው ይመሰክራል ።

ከዚህም በላይ አንድ ጊዜ ቅዳሴውን ደግመው ውኃውን ቢባርኩት ኅብስት ሆኖላቸው ራሳቸው



www.ethiopianorthodox.org

ተመግበው አብረቻቸው የነበሩትንም ምእመናን መግቧቸዋል ይላል ።

እንግዲህ የወርቅ ጥሩንትና ግብዝነት የሚታወቀው በእሳት ከተፈተነ በኋላ እንደ ሆነ በሁላችን የታወቀ ነው እንግዲያስ የሃይማኖትም ጽናት የሚታወቀው በገድል መሆኑ ልንገነዘብ ይገባል ።

አሁንም ቢሆን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን ተከትለን እርስዋ በምትመራው ስነ ሥርዓት ጸንተን የምንኖረው እንዲሁ በከንቱ አይደለም

በክርስቶስ የተመሰረተች በሐዋርያት የተሰበከች በሁሉም ዘንድ ሕፀፅ የሌለባት መሆንዋን በማመን ነው ስለዚህ እነ አቡነ ሳሙኤልን ያስገኘች ሃይማኖት ወደ ክርስቶስ የምታቀርብና ሰማያዊ ዓለምን የምታወርስ መሆንዋን አውቆ ሁሉም በኦርቶዶክሳዊት ተሕዋዶሃይማሃኖት መጽናት አለበት ያለ ይማኖት ሕይወት አይገኝምና ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

# ዘመነ ስብከት

ለሁሉም ጊዜ አለው ፤— ዘር ለመዝራት የተዘራውንም ፍሬ ለመሰብሰብ ወቶተ እንዳለው ሁሉ ለመሰብሰብም ለማስተማርም ጊዜ አለው ይኸውም በታህሣሥ ወር ከመጀመሪያው ሳምንት ቀጥሎ ክርስቶስ ከመወለዱ አስቀድሞ ነቢያት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን ከኃጢአትና ከኩነኔ እንደሚያድን ትንቢት የተናገሩበት ወቅት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ይህን በማዘከር ሳምንቶቹን ስብከት ፤ ብርሃን ፤ ኖላዊ ፤ ብላ በመከፋፈል የተነበዩለትንና የሰበኩለትን ሐዋርያትም የመሠከሩለትን የዓለም ብርሃን እረኛ አዳኝ የሆነውን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትሰብካለች ታስተምራለች ።

ሊቀነቢያት ሙሴ ሐመልማል ከነበልባል ነበልባል ከሐመልማል ተዋሕዶ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉም ነበልባሉን ሳያጠፋው አይቷል ይኸውም የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም መገለጹን የሚያመለክት ነው ።

አዳም የአምላኩን ሕግ በመጣሱ ከአምላኩ ተለየ ተረገመም ጠላት ዲያብሎስም በእባብ ሰውነት አድሮ ድል ስለነሣው የእርሱ ባሪያና ተገዢ እንደሆነ ሲተወው አልፈለገም ሰይጣን የእባብን ሥጋ ለብሶ ሥጋ ለባሲ የሆነውን አዳምን ቢያሸንፈውም እግዚአብሔር ደግሞ የሰውን ሥጋ ለብሶ ከእመቤታችን ተወልዶ ረቂቁን ጠላት ዲያብሎስን ራሱን እንደሚቀጠቅጥለትና ነጻ እንደሚወጣው የታመነ ተስፋ ሰጠው በተስፋውም መሠረት ገና በበደልና በኃጢአት ውስጥ ሳለን አንድ ልጁን ልኮ በደላችንን ተሸክሞ የእዳ ደብዳቤያችንንም መቶ እንደሚደመሥሰው ትንቢት ተነበየ ስብከትም ተሰበከ ኢሳ ፱፡ ፭—፲፪ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሚያድነንም ትንቢት ተናገረ ኢሳ ፯ ፡ ፲፬

ሌሎችም ነቢያት ስለዚህ የተስፋ ቃል በብዙ ቦታ ተንብየዋል ሰብከዋልም የነቢያትም ትንቢትና ስብከት እየደመቀና እያበራ መጣ በዚህም ምክንያት ክርስቶስን«ብርሃን»ብለው ጠሩት በጨለማ የኖረ ሕዝብ ብርሃን አየ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው ኢሳ ፱ ፡ ፪ ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረ ነቢያት በትንቢታቸው የተነበዩለት እውነተኛው የጸድቅ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ በኃጢአት ጨለማ ውስጥ ለነበሩ ብርሃንን በሰይጣን ቀንበር ውስጥ ለነበሩት ነጻነትን ሰበከላቸው ።

ይመጣል ተብሎ የተሰበከለት ይህ የጽድቅ ብርሃን የሆነ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛና የዘለዓለም ብርሃን ነው ያመኑትና የተቀበሉት ሁሉ በብርሃኑ ይኖራሉ በብርሃኑም ይመላለሳሉ ለምሳሌ ወደብርሃን ስንጠጋ ጨለማ የጋደረውን ማስተዋል እንደምንችል ሁሉ ወደክርስቶስም ስንጠጋ የኃጢአት ጨለማ ጋርዶብን የነበረውን ሁሉ እናስተውላለን ።

በዘመናችን አንዳንድ ወገኖች ይህ የሕይወት ብርሃን ያልበራላቸውና ገና በጨለማው ዓለም ውስጥ እንደተዋጡ ያሉ ቀኑ ሳይጨልም የጨለመባቸው የኑሮ ትርጉም የጠፋባቸው የዓለም ኑሮ ምስቅልቅል ብሎ ያስቸግራቸውና ከሕይወት ይልቅ ሞትን የመረጡ ወገኖች እጅግ ብዙዎች እንደሆኑ እናውቃለን እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ማቴ ፭ ፲፬ ተብሎ ስለተነገረ በብርሃኑ ያመኑ ሁሉ እንደዚህ ባለው ዓለም ውስጥ እየገቡ የክርስቶስን ብርሃንነት ማንጸባረቅና ትርጉም ያጣውን ሕይወት በወንጌል ስብከት ማጣፈጥ ግዴታና ኃላፊነትም ጭምር አለበት የሚል ይህም የማንኛው ክርስቲያን ሕይወት መብራት የሚገባውን የሕይወት ብርሃን እንዳበራ እንቅብ ሊደፋበት አይገባም ።



በሌላ መንገድ ስንመለከት ክርስቶስ ኖላዊ መልካም እረኛ ሆኖ እናገኘዋለን (መዝ ፩፻፳ ፣፫፻፲፮) ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይለናል እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ እፈልግማለሁ እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑበት ሥፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸዋለሁ የጠፋውንም እፈልጋለሁ የበዛነውንም እመልሳለሁ ለደከመውንም አጸናለሁ« ሕዝ ፴፬፩—፳፬»በማለት ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለነበሩት እሥራኤላውያን እረኞች ድክመት ሲገልጽ በአንጻሩ ስለእውነተኛው እረኛ ሙያተኛ ስላልሆነው ይመጣል ተብሎ ስለተሰበከለት ስለጌታችንና ስለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰፊው ጽፏል ።

ምንም እንኳን እረኞች በተለያየ ምክንያት የተሰጣቸውን አደራ ባይጠብቁም እግዚአብሔር ግን መንጎቹ እንደተበተኑ ለተኩላ እንደተሰጡ የሚተው አምላክ አይደለም በእውነትም የጠፋው የባዘነውን የሚመልስ እውነተኛና ጻድቅ የሆነውን ለበጎቹም ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከው እንዳለፉት እረኞች ከበጎቹ ምንም የሚያስፈልገው ነገር አልነበረም ያለምንም ዋጋ በክቡር ደሙ ሊዋጅ መጣ ።

ስብከትና ትምህርት በነቢያት ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር ከየነገዱና ከተለያየ የሥራ ቦታ እርሱን የሚከተሉ ደቀ መዛሙርትን መረጠ የእረኝነትንና ስብከትን ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ሙሉ አንድ በአንድ አስተማራቸው እነርሱም ከተማሩና መጨረሻም መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ዓለምን ዳር እስከዳር በስብከታቸውም ሞኋት ብዙዎች የባዘኑትንና የተቅበዘበዙትን ወደ ክርስቶስ መለሳቸው ይህም የስብከትና የእረኝነት ሙያ ሲወርድ ሲዋረድ ከእኛ ደርሷል የእኛ የእረኝነት ጠባይ በዘመናችን መንጋው ብዙ ስለሆነ በመንፈስ የተቀኙ እረኞች ያስፈልጋሉ የመንጋው ባለቤት እረኞችን እንዲልክ የመጠየቁ ጉዳይ ግን የሁላችንም ነው ።

እንደነቢያትና ሐዋርያት በእግዚአብሔር መንፈስ የተላከ ሐዋርያ ያስፈልጋል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል«ማንንእልካለሁማንስይሄድልናል ኢሳ ፮፡፰ ዛሬ ሁሉም ራሱ በደበቀበት ዘመንና ዓለም በኃጢአት በተጥለቀለቀበት ወቅት በኢሳይያስ ዘመን እንደሆነ ዛሬም እግዚአብሔር አምላክ ወደሕዝቡ የሚልከውን መልእክተኛ በፈቃደኝነት የሚስብ ሐዋርያ ይጠራል ይህ ጥሪ ለሁላችንም መሆኑን እየተረዳን ፈቃደኛ አለመሆን ተቀባይነት የሌለውና ያልሆነ ምክንያት ይዘን የምንቀርብ አልጠፋንም ለምሳሌ ወጣት ነኝ አልተማርኩም የቢሮ ሠራተኛ ነኝ የቢሮ ሥራ ካል ሆነ በቀር ስብከት ስጦታዬ አይደለም ባደባባይ ቆሞ ማስተማር መመስከር አልችልም - - - ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው እግዚአብሔር ግን ወደምሰድህ ሁሉ ትሄዳለህና የማዝህንም ሁሉ ትናገራለህና ብላቴና ነኝ አትበል» ኤር ፩ ፤ ፍ—፰ ይላል በተለያየ ሥራው ስተሠማራው የዓለም ሕዝብ በዚያው እንጻር የተሰማሩ ሐዋርያት ሰባክያን ያስፈልጉታል ተና ጋሪውና መምህሩ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ከሰው የሚፈለገው መልስ በጎ ፈቃደኝነትና «ጌታ ሆይ እኔን ላከኝ» በማለት ብቻ ነው መጽሐፈ ቅዱስ ሌላው ቀርቶ ባልቴቶችን እንኳ ብዙ ጊዜ ለእግዚአብሔር መልእክት መሣሪያዎች እንደሆኑ ይናገራል ፤ ነገሩን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ፡ ንዳንዶቹን ለመጥቀስ እወዳለሁ ሳሙኤል እግዚአብሔርከካህኑከኤሊ ይልቅ ብላቴናውን ሳሙኤልን ጠርቶ ለኤሊ መነገር የሚገባውን መልእክት በብላቴናው በኩል ላከው (ሳሙ ፫ ፡ ፩—፲፬ ።

ዳንኤል ረበናተ አይሁድ መምህራን የሕዝቡን ኃጢአት እንዲያስተሠርይልን እያሉ የሚታበዩትበ ሶስና ላይ ተነሣሥተው ተንኮላቸውን ለመፈጸም ባለመቻላቸው ተቆጭተውና ተናድደው በሕዝብ አደባባይ ላይ በሀሰት አስመስክረው የሞት ፍርድ ከፈረዱባት በኋላ እግዚአብሔር ግን ፈታሂ በርትዕ ኰናኒ በጽድቅ ስለሆነ ብላቴናውን ዳንኤልን ላከ ዳንኤልም ማንም ሳይሆን እግዚአብሔር በሰጠው ሥልጣን ፈራጆቹን የአይሁድ መምራንን መርምሮ በፈረዱበት ፍርድ እንዲያዙና በክፉ አሟሟት በመልአክ እግዚአብሔር ተቀስፈው እንዲሞቱ አደረገ ።

፫ቱ ደቂቅ ናቡከደነጾር ላቆመው ምስል በእምነት ከመጽናታቸው የተነሣ «አንሰግድም» በማለታቸው ከእቶን እሳ ት ውስጥ ከመዳናቸው ሌላ ራሱ ናቡከደነጾር ለእግዚአብሔር እንዲያምንና የእግዚአብሔር ስምም እንዲከበርና አዋጅ እንዲታወጅ አስደረጉ እነዚህንም ሆነ ሌሎችን አስነስቶ ስሙን ያስመሰገነ አምላክ በዚህ ሐዋርያ አስነሥቶ ስሙን ለማስመስገን ኃይሉን ለመግለት አይሳነውም ።

ስለዚህ ያለንበት ወራትና ዘመን የስብከት ዘመን በመሆኑ ምክንያት ሳንፈጥር ሁላችንም ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ራሳችንን ልናዘጋጅ ይገባናል ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ተብሎ ተጽፏልና ።

ዲ/ገዳሙ ደምሣሽ



www.ethiopianorthodox.org

# ተአምራዊ ዜና ፤

የእመቤታችን የቅዱሳን መላእክትና የጻድቃን ሰማዕታት ተአምራት በየጊዜያቱ እየቀጠለ ነው። በተለይም በሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ጠበል የሚ ፈጸመው ገቢረ ተአምር ያለ ማቋረጥ እየቀጠለ ነው

ይኸውም ፩ኛ/ ወ/ሮ በላይነሽ የተባሉ ሴት
፪ኛ/ የሽጥላ በላይ የተባለው ወጣት ሽባ ሆነው ለብዙ ዘመናት ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ ዘመዶቻቸው በእልጋ ተሸክመው ወደዚሁ ጠበል አምጥተው እንዲጠመቁ በማድረጋቸው ነሐሴ ፳ ቀን እና ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በእመቤታችን አማላጅነት ከያዛቸው አሰቃቂ ደዌ ሊድኑ ችለዋል።

እንዲሁም በከፍተኛ ፲ ቀበሌ ፲፯ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ቀለሟ አስቻለው ለሦስት ወራት ያህል ጆሮአቸው ከመስማት ተከልክሉ በስቃይ ሲኖሩ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሽተኛዋ በሚያውቋቸው ወ/ሮ ብርሃኔ በሚባሉ ሴት ተመስላ በሕልማቸው ወደ እርሳቸው ትመጣና ወደ ኪዳነ ምህረት ሄደሽ ካህናቱ ቅብዓ ሜሮን በጆሮሽ ካደረጉልሽ በኋላ ጠበል ተጠመቂ ብላ ስለነገረቻቸው ወደ ኪዳነ ምህረት ሄዱ ።



በኪዳነ ምሕረት ጠበል ከሽባነት የተፈወሱት ወ/ሮ በላይነሽ እኚህ ናቸው ።

ወ/ሮ ቀለሟ እንደተነገራቸው ካህናቱ ወደ ኪዳነ ምህረት ሄደው ቅብአ ሜሮን እንዲያደርጉላቸው ጠይቀው ካደረጉላቸው በኋላ ከጠበሉ እንደተጠመቁ ሁለቱ ጆሮአቸው ተከፍቶላቸው እንደ ጥንቱ ለመስማት መብቃታቸውን የገዳሙ አስተዳዳሪ መምህር ላዕከ ማርያም አየለ ገልጸዋል

ከዚህም ሌላ በከፍተኛ ፳ ቀበሌ ፵ ነዋሪ የ፳ ዓመት ወጣት የሆነው ዘውዱ አሰፋ በዚሁ ጠበል ተጠምቆ ከጠጣ በኋላ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ፲፱ እባብ መሰል አውሬ ዎች ከሆዱ ስለ ወጡለት ሊፈወስ ችሎአል ።

ዘውዱ አሰፋ ይህ አሰቃቂ በሽታ መቼ እንደ ጀመረውና ሁኔታው እንዴት እንደሆነ አብራርቶ እንዲያስረዳን ላቀረብንለት ቃለ መጠይቅ ሲመልስ በሽታው በቁርጠት መልክ የጀመረኝ በመጋቢት ወር ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ነው አውሬው በሆዴ ውስጥ ከግራ ወደ ቀኝ እየሮጠ በሚያስፈራ ድምጽ ይጮኽ ነበር ብሎአል ።



በኪዳነ ምሕረት ጠበል ፲፱ እባቦች የወጡላቸው ወጣቶች ።

ወደ ኪዳነ ምሕረት ጠበል ሄዶ ሲጠመቅና ሲጠጣ ቆይቶ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የሆድ መታወክ ገጥሞት ከዓይነ ምድር እንደተከተመጠ ወዲያውኑ አንድ እባብ ከሆዱ ከወጣ በኋላ ተፈትልኮ ሜካ እንደገባና ሌሎቹ ፲፰ እባብ መሰል ቅርጽ ያላቸው አውሬዎች ደግሞ ተከታትለው ስለ ወጡልኝ ከያዘኝ በሽታ ልገላገል ችያለሁ ሲል ቃሉን ሰጥቶአል ።





በኪዳነ ምሕረት ጠበል ከዘውዱ አሰፋ ሆድ የወጡ ፲፱ እባብ መሰል አውሬዎች ።

በከፍተኛ ፲፰ ቀ ፲፭ የቤ ቁጥር ፫፻፶፭ ነዋሪ የሆነ ተማሪ ጌታሁን አብርሃ እንዴት እንደተፈወሰ ሲያስረዳ የበሽታዩ ዓይነት የሆድ ቁርጠት ሲሆን ሁኔታውን ግን ማቃጠል ማኘሁ ነው በሽታው ከያዘኝ ከስድስት ዓመት በላይ ነው ። መጠመቅ የጀመርሁት በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ነው ።

ከጠበሉ በምጠመቅበትና በምጠጣበት ወራት ቀኑ ትዝ አይለኝም እንጂ አረንጓዴ ዓይነት ከብ የሆነ የትል ቅርጽ ያለው አውሬ ወጣልኝ ሁለተኛ ብሜና ሞራ የመሰለ ነገር በድጋሚ ወጥቶልኛል ከመጠመቁ በፊት በሽታው ሲነሳብኝ ያጮኸኝ ነበር እህል ም ፈጽሞ አልቀምስም ነበር ። በቤተ ሰቤ አካባቢ ብዙ ችግር ሲፈጥርብኝ ነበር ። ከተጠመቅሁና ከጠበሉ ከጠጣሁ ጀምሮ ግን ዳቦና ወተት የመሰለ ለመብላት በቅቻለሁ ። ይሁን እንጂ አሁንም ፈጽሞ ስላልተሻለኝ እጠመቃለሁ ።

በይበልጥም የበሽታ ጓደኛዩ ሳይሰለቸው ተግቶ በመጠመቁ ምክንያት የመጨረሻ ፈውስ ለማግኘት እንደቻለ ሁሉ እኔም እምነቴን በማጠናከር እስከ ዳንሁ ድረስ ሳላቋርጥ ለመጠመቅ ስለወሰንሁ ልፈወስ በቅቻለሁ ብሎአል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የመጀመሪያው ተአምር

የዓለም መድኅን ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዕሪና የነበረ የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ በአንድነትና በሦስትነት ሲሠለስ የነበረና ያለ የሚኖርም ዘለዓለማዊ አልፋና ኦሜጋ ነው (ራእ ፩ ፡ ፰ ፤ ምዕ ፳፪ ፡ ፲፫) ከዓለም ፍጥረትም አንሥቶ በየዘመናቱ በአንዳንድ ምርጥ አገልጋዮች አድሮ ብዙ ታምራት (ድንቅ ሥራዎችን) ሁሉ ሲሠራና ሲያሠራ የሚኖር ምሥጢር እንደእንግዳ ደራሽ እንደውሃ ፈሳሽ አዲስ የተጀመረ ሳይሆን ከዚያው ከጥንታዊ መለኮታዊ ሥራው ጋር ተጣምሮ የሚታይ ነው ።

ይህ በዚህ እንዳለ በዮሐንስ ፪፥ ፩—፲፩ በተጻፈው መሠረት በ፮ የድንጊያ ጋኖች የተሞላውን ውሃ ወደ ወይን ጠጅነት የመለወጡን ድንቅ ሥራውን የመጀመሪያ ተአምር ያሰኘው ለቤዛ ዓለም በፈቃዱ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ አምላክ ወሰብእ ሆኖ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተገልጦ እንደሰው ይመላለስ በነበረበት ጊዜ የወንጌሉን ቃል ማስተማር ሲጀምር ለዚያ መጠናከሪያ የሆነውን ይህን ተአምር በሠርግ ቤት በማድረጉ ነው እንጂ ከዚያ በፊት ያልነበረውን ተአምር የማሳየት ጉዳይ አይደለም ።

ከሌሎች ተአምራት ሁሉ የተለየ የሚያደርገውም ሌላው አስደናቂ ነገር በጥንተ ተፈጥሮ የኅብረተሰቡ ሥርዓት መጀመሪያ አድርጎ ያከበረውን የተቀደሰ ጋብቻ አሁንም የተአምራቱ መጀመሪያ ማድረጉ ነው ።

የውሃው ወደወይን ጠጅ የመለወጥ ምሥጢር ሌላም አስደናቂ ትርጉም አለው ። ይኸውም ክርስቶስ የሰውን ሕይወት በመለወጥ አዲስ ፍጥረት ማድረግ የሚችል መሆኑን ያበሥራል ። ፪ኛ ቆሮ ፭ ፣ ፲፯

ከዚህም ሁሉ ጋር በዚሁ መለኮታዊ ተአምር የምናየው ታላቅ ሥራ ክርስቶስ ያለበት ማለትም የክርስቶስ ስም የሚጠራበት ጋብቻ ሁሉ ምን ያህል ታላቅ በረከት እንደሚገኝበት የሚያመለክት ነው ። የቃና ዘገሊላው ሙሽራ ዶኪማስ በራሱ ወይም ከወላጆቹ መልካም ፍላጎትና ፈቃድ እመቤታችን ቅ/ድንግል ማርያምን ልጇዋን የዓለም መድኅን ክርስቶስን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቶ በሠርጉ ድግስ ላይ እንዲገኙለት ማድረጉ የዚያ መለኮታዊ በረከት ባለቤት ለመሆን አብቅቶታል ። ይኸውም የወይን ጠጅ አልቆ ጋን ማድጋው ደርቆ ቤተሰብ ችግር ላይ ወድቆ እንደነበር በእመቤታችን አነጋገር ታውቋል እርሱም «ወይን ጠጅ የላቸውም አልቆባቸዋል» የሚል ነበር ጌታም ፊት የሚያስመልስ አንገት የማያስቀልስ ልመናዋን ሰምቶ ስድስቱ የድንጊያ ጋኖች ውሃ እንዲሞላባቸው አዘዘ ታዲያ ሙሽራው ዶኪማስ ከነበረው ሌላ መልካም ዕድል ትእዛዝ ፈጻሚዎቹ አገልጋዮች አስተናባሪዎች የነበሩት በመሆኑም ይደነቃል ። ታዛዦች ሆነው በመገኘታቸው ስድስቱን የድንጊያ ጋኖች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ውሃ ሞሉ ፤ ክርስቶስም ያንን ውሃ ወደወይን ጠጅ በመለወጥ የመጀመሪያውን ተአምር በማሳየቱ «ደቀ መዛሙርቱ አመኑበት» ተብሎ ተጽፎአል ። ስለዚህም እኛም ሁላችን ለክርስቶስ ቃል ታዛዦች ሆነን ብንገኝና እርሱ የሚለንን ሁሉ ብንፈጽም በያንዳንዳችን ሕይወት የመለወጥ ተአምር የመሥራት ኃይል አለው ።

የገሊላ አውራጃ ክፍል በሆነችው በዚያች በቃና መንደር ተደርጎ የነበረው ሠርግ ዓይነት ዛሬም በዓለማችን በብዛት እየተፈጸም ነው ብዙ ክርስቲያኖች የጋብቻቸው ሥርዓት በክርስቶስ የተባረከ እንዲሆን በተክሊልና በሥጋ ወደሙ በመፈጸም ላይ ናቸው በርሱም ታላቅ በረከት አግኝተው የተባረኩ ልጆች ወልደው ከብረው የሚኖሩ አሉ ። ይህም የታላቅ ክርስቲያንነት ዓርማ ነው ። ክርስቶስ ራሱ ሲናገር እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይችልም በማለት (ማቴ ፲፱ ፡ ፩—፱) ቀድሞ በጥንተ ፍጥረት «ሰው አባቱንና እናቱን እንኳ ትቶ ከሚስቱ ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ይሆናል ተብሎ (ኦሪት ዘፍጥ ፪ ፡ ፳፬) የተጻፈውን ቃል እንደገና በማደስ ድርብ ጋብቻንና የመፋታትን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል ።

ቤተ ክርስቲያንም ስለ ቅዱስ ጋብቻ ያላት ሥርዓት ሁሉ በዚሁ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ «ጋብቻ በሁሉ ዘንድ የከበረ ይሁን» ተብሎ በሐዋርያው ጳውሎስ የብርዕ አንደበት የተናገረው (ዕብ ፲፫ ፡ ፬) በዘመናችንም ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ። አሁንም ቸርነቱና ስጦታው የማያልቅበት ሕያው አምላክ ክርስቶስ በቅዱስ ስሙ የተመሠረተውን ክርስቲያናዊ ጋብቻ ሁሉ በመባረክ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት የሠራውን ድንቅ ተአምር ደግሞ ይሠራው ዘንድ ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን ። አሜን

ቄ/ መክብብ አጥናው



# «ሰላም በምድር ! !»

«ሰላም በምድር» የሚለው ቃል ሰዎች በሰው ሰውኛ/ በዲፕሎማሲ/ ማኅበረ ሰብእን ለማቀፍ ማለትም አብሮ ለመኖር ይበጃል ተብሎ የሆድን በሆድ አስቀምጦ የዚህ ዓለም ሰዎች በሽንገላ በሚጠቀሙበት ዘዴ በምድራውያን ሰዎች የተነገረ ሳይሆን በሰማይ ሠራዊት ነበር የተነገረው ወይም የተላለፈው ። መቼና እንዴት አስተላለፉት? ወደሚሉትያቄዎች ከመግባታችን በፊት ይህ መልእክት ከመደረሱ አስቀድሞ ሰላም በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል አልነበረምን? በፈጣሪና በፍጡር መካከል ሰላም እንዳይኖር ያደረገ ኃይልስ ምንድነው? በምድራውያን ሰዎች መካከል ሰላምን ያሳጣ ጠላትስ ማን ነበር? ወደሚለው ጥያቄ ገባ እንበልና በመጠኑ ሐሳቦችንን በማንቀሳቀስ እንመርምር ።

ምርምራችን እውነትን የተከተለና በማያረካ ምክንያት ያልተድበሰበሰ ከሆነም ሰላምን ያሳጣው የሰው ልጅ ጠላት የራሱ ፍላጎት (ግላዊ ምኞቱ) ሆኖ እናገኘዋለን ። አይደለም የሰው ልጅ ጠላት ዲያብሎስ (አባብ) ነው የሚል ተከራካሪ እንደማናጣም እናውቃለን ፤ ነገር ግን ዲያብሎስ (አባብ) ለሰው ልጅ ፍላጎት ማርኪያ መሣሪያ ሆነ እንጂ ባለቤት ሆኖ አናገኘውምና በሐሳባችን እንጸናለን ።

ይህ ምርምራችን ከቅዱስ መጽሐፍ ቃልና አሁን ከሚታየው የሰው ልጅ በሕርያዊ ምግባር ፈቀቅ ስለማይል እውነትነቱ ጉልህ ሆኖ የሚታይ ነውና በአስተዋይ ሕሊና ተቀባይነት እንደሚኖረው እንተማመናለን ።

ከቅዱስ መጽሐፍ እንጥቀስ ፤

ሀ/ ጠቢቡ ሰሎሞን «የሰውን ልጅ ተፈጥሮ በእግዚአብሔር አምሳል በሕይወት ለመኖር ስለሆነ ፡ እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም ። ነገር ግን ሰነፎች ሰዎች መረጡት በቃላቸውም ጠሩት ፤ ጓደኛም አደረጉት ። »ይላል ።

ለ/ ነቢዩ ሙሴም በኦሪት ዘፍጥረት የሰው ልጅ የፍላጎቱ ተገዢ መሆኑን ሲገልጽ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ሲል አዘዘው ፤ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስተዋውቀው ዛፍ አትብላ ። ከእሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ።»በማለት ካዘዘውና ካስጠነቀቀው በኋላ ለፍላጎቱ ማርኪያ ሲል ትእዛዙን እንደጣሰ ማስረጃውን ሲያጎላው «እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አራዊት ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ ሴቲቱንም በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት ።

ሴቲቱም ለእባቡ እንዲህ አለችው «በገነት ካለው ዛፍ ፍሬ ሁሉ እንበላለን ፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ እንዳንበላ እግዚአብሔር አለ ፤ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።» እባብም ለሴቲቱ አላት ፤ «ሞትን አትሞቱም ከእርሱ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንደሚከፈቱ መልካምንና ክፉን እንደምታውቁ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ ።

ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም እንደሚበጅ (መልካም እንደሆነ) አየች ከፍሬውም ወስዳችና በላች ፤ ለባልዋም አበላችው ፤ እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ ። የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ ። እንግዲህ ሁለቱም የፈለጉት ይህ ነበር ፤ ማለት የማያውቁትን ለማወቅ ጉጉት ነበራቸውና ዕርቃናቸውን መሆናቸውን አወቁ ፤ በዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካችን ውስጥ እንደተመለከትነው «መልካምንና ክፉን የሚያስታውቅ» የሚለው ሐረግ የሚያጓጓ ሆኖ ፤ ለመብላት የሚያምር ፤ ለዓይን የሚያስጎመጅ ለጥበብ የሚበጅ የሚሉት ሐረጎች ሁሉ የሚያስጎመጁ እንደሆኑ እንመለከታለን ።

ስለዚህም አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ሁለቱም ያላወቁትን ለማወቅ ፤ አምላክነትም ለመሆን ጓጉተው ከመካከላቸው ገላጋይ ሳይኖር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመጣስ ተባበሩ ፤ ለፍላጎታቸው ብቻ ተገዙ ።

በዚህ ጊዜ ይታዘዟቸው የነበሩት እንስሳት አራዊት ሁሉ ከዷቸው ፤ ቀንዳቸውና ጥፍራቸውን አሾሉባቸው ፤ ዓይናቸውን አፈጠጡባቸው ጥርሳቸውን አገጠጡባቸው መድረሻ አሳጧቸው ይታዘዙአቸው የነበሩት መላእክት ሰይፈ መዓታቸውን መዘው ከሚወዷት ገነት አባረሯቸው ።

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሰላም (የፍቅር የአንድነት)ግንኙነት እንዳይታይ ትልቅ የጸብ የኃጢአት መጋረጃ ተጋረደ ።

ዲያብሎስ ከክብሩ ተዋርዶ ሲወድቅና ለአዳምም መላእክት ሲያገለግሉት ሲመለከት በምቀኝነት ተመልቶ አሁንም የሌለውን አምላክነት ፤ ሽቶ በጉጉት እንዲማቅቅ ለፍላጎቱ ማርኪያ መሣሪያ ከሆነና አዳምም ከተዋረደ በኋላ ምን ያህል ደስ እንደሚለው ሕሊናችን ያስገነዝበናል ። «ባለጌ እሱ በገበረለው አያዝንም ወንድሙ በቀረ» ይባል የለ? መቼም ምቀኛ ጎረቤቱ በሰላም ከሚኖር ጎረቤቱ ገደል ገብቶ



www.ethiopianorthodox.org

እሱ ቢኖር ደስ ይለዋል ። አንድ ታሪክ እንጥቀስ ፤

«አንድ ሰው እግዚአብሔርን አፈልጋለሁ አለና ሱባኤ ገባ ፤ በበአቱ ሁኖ ሲጸልይም እግዚአብሔር ጸሎቱን ተቀበለለትና በግልጽ ታየው ። «የምትፈልገውን ንገረኝና አደርግልሃለሁ ፤ ላንተ ያደረግሁልህንም ለጎረቤትህ አደርግለታለሁ ።» አለው ። ታዲያ ሰውየው ምቀኛ ነበረና እሱ ተጠቅሞ ጎረቤቱ ከሚጠቀም ይልቅ እሱ ተጎድቶ ጎረቤቱ እንዲጠፋ በመምረጥ «ለእኔ ያደረግህልኝን ለጎረቤቴ የምታደርግለት ከሆነስ አንድ ዓይኔን አጥፋልኝ» አለው ።

ያጎረቤቱ አንድ ዓይና ኑሯል ፤ ስለዚህ እሱ በአንድ ዓይን ሲጠቀም ጎረቤቱ ግን ጨርሶ እንዲታወር ያደረበትን ምኞት ሲያንጸባርቅ ነው ።

እንግዲህ «ሰላም በምድር» መቼና እንዴት ተሰበከ? ወደሚለው ጥያቄ እንመለስና አዳምና ሔዋን በዚህ ስሕተታቸው ተጸጽተው ንስሐ ገብተው ስላለቀሱ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ቃል የአዳምን ሥጋ ለብሶ እንደሚታረቀው ሲያስረዳ ዜና እስክድር እንዲህ ይላል ። «ይቤሎ መንፈስ እግዚአብሔር (መሰቀሉን ሲያስረዳ) ዘውእቱ ቃል ዘአስተርአዮ በአምሳለ መልአክ ለእስክንድር በመልአክ አምሳል የታየው የእግዚአብሔር መንፈስ ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል ለእስክንድር እንዲህ አለው ። «ለእመ በጽሐ ዘመኑ ለዕለትየ በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እለብስ ሥጋሁ ለአዳም በእንተ ዕልወቱ የምወለድበት ዘመን በደረሰ ጊዜ በአምስት ቀን ተኩል የአዳምን ሥጋ እለብሳለሁ ስለበደሉ ንስሐ ገብቶ ባደረገው ጸሎት» ይላል። ዜና እስ ፤ ፤

አምስት ቀን ተኩል ማለት አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ማለት መሆኑ ነው ። አዝሲማምስት መቶ ዘመን ማለት መሆኑ ነው ። አክሲማርስ የተባለ መጽሐፍ ሰማይና ምድር ከተፈጠሩበት ዕለት ከዕለተ እሑድ ጀምሮ አዳም እስከ ተፈጠረበት ዕለተ ዐርብ ድረስ ያለው ዘመን ስድስት ሺህ ዘመን መሆኑን ያረጋግጣል ። በዚህ አቈጣጠር (የስሌት) ያሳነን እንደሆነ ከገነት በላይ ያሉት የአስር አበው ዘመን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሁነው እናገኛቸዋለን ።

ከሙሴ ጀምሮ እስከ ሚልክያስ የነበሩት አበው ነቢያት «እግዚአ አምላክነ ሰላመ ሀበነ» አቤቱ አምላካችን ሰላምን ስጠን በማለት ይጸልዩ ነበር ። አምላካችን ሰላምን ስጠን በማለት ይጸልዩ ነበር ። አምላክም ጸሎታቸውን በመቀበል ነቢያትን የሰላም አምላክም ጸሎታቸውን በመቀበል ነቢያትን አስነሥቶ «ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ» እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራታለች ፤ ዘበትርጓሜው እግዚአብሔር ምስሌነ ፤ አማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው ። በማለት አስቀድሞ ትንቢት ያናግርና ተስፋውን ያረጋግጥ ነበር ። ኢሳ ፯ ፤ ፲፬ ፤

ጊዜውም በደረሰ ጊዜ የሰላም አምላክ ናዝሬት ወደምትባል የገሊላ ክፍል ወደምትሆን ሀገር መልአክ ሰላም ቅዱስ ገብርኤልን ላከ ። በዚህ ም ናዝሬት በምትባለዋ ትንሽ ከተማ ከዳዊት ወገን የተወለደ ዮሴፍ የሚባል ሺማግሌ የሚጠብቃት ድንግል ማርያም ነበረች ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም ቀረብ ብሎ «ጸጋን የተመላሽ ድንግል ሆይ! ደስ ይበልሽ ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ በለሟልነትን አግኝተሻልና ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ እሱ ታላቅ ይሆናል ፤ የልዑል ልጅም ይባላል ፤ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም አላት ። ድንግል ማርያምም እኔ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? መሬት ያለዘር ማብቀል ሴት ያለወንድ መውለድ ይቻላልን? በማለት ጠየቀች ።

መልአኩም «መንፈስ ቅዱስ ወዳንቺ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል ፤ ከአንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው የእግዚአብሔር ልጅም ይባላል» ካለ በኋላ መካንዋ አክስትሽ ኤልሳቤጥ እንኳ ካረጀች በኋላ ጸንሳለች ። እነሆ አሁን ስድስት ወር ሁኗታል ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለውምና» አላት ።

እሷም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም የሚለውን ጎረና ስትሰማ ያለ አንዳች ጥርጥር አምና በመቀበል እነሆ የእግዚአብሔ አገልጋይ ነኝ እንዳልኸው ይሁንልኝ» አለች ።

በዚህ ጊዜ እኛ ሰዎች ማስረዳት በማንችልበት አምላካዊ ምሥጢር የእግዚአብሔር ቃል ተጸነሰ ፤ ሥጋን ለበሰ ። በዚያም ወራት ሰው ሁሉ እንዲመዘገብ ( የሰው ቍጥር እንዲታወቅ) ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣ ። እያንዳንዱ ሰውም ይጻፍ ዘንድ ወደ የከተማው ሔደ ። የድንግል ማርያም እጮኛ (ጠባቂ) ሺማግሌው ዮሴፍም ከእጮኛው ከድንግል ማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ገሊላ ክፍል ከምትሆን ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ወደ ዳዊት ሀገር ወደ ቤተልሔም ተጓዘ ።

በቤተ ልሔም ሳሉም የመውለጃዋ ቀን ደረሰ ፤ በድንግልና የጸነሰችውንም አሁንም በማይመረመር ምሥጢር በድንግልና ጌታ ኢየሱስን ወለደች ። የሚያርፉበት የእንግዳ ቤት ስንኳ ባለመገኘቱ በከብቶች በረት ውስጥ ነበር የተወለደው ፤ ስለዚህም በጨርቅ ጠቅልላ በግርግም አስተኛችው ።

በዚያም ሌሊቱን ሁሉ ከብቶቻቸውን በትጋት ሲጠብቁ ያደሩ እረኞች ነበሩ ። እነሆም የጌታ መልአክ ወደ እነሱ ቀረበ ፤ የጌታ ክብርም በዙሪያው አበራ ። እረኞቹም ታላቅ ፍርሃት ፈሩ ።



መልአኩም አይዟችሁ ፤ አትፍሩ ፤ እነሆ አሁን ደስ የሚያሰኛችሁን ለዓለም ደስታ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እንግራችኋለሁና እነሆ መድኅን ተወልዶላችኋል ፤ እሱም ጌታ ክርስቶስ በዳዊት ሀገር ፤ ምልክት እነሆ ሕፃን ተጠቅልሎ ፤ በግርግም ተኝቶ ታገኙላችሁ ፤ አላቸው ። ይህንም በሚነግራቸው ጊዜ ድንገት ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ፤ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ እያሉ ተሰሙ ፤ ተገለጡም ።

ጌታ ኢየሱስ በተወለደበት ቅጽበት በመላእክት አንደበት «ሰላም በምድር» የሚለው ስብከት ተሰበከ ፤ ይህ ሰላም የሚባለው ቃል ፍቅር አንድነት ማለት መሆኑንም ከላይ ከመግቢያችን በመጠኑም ቢሆን ገልጸናል ።

ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቱ «እግዚአብሔርን እወዳለሁ ። የሚል ፤ ጓደኛውን (የተፈጥሮ ወንድሙን ) የሚጠላ ዋሾ ነው ፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና በማለት ያስተላለፈውን መልእክት ከዚህ ከመላእክት መልእክት ጋር በማነጻጸር ስንመለከት ሰላም ፍቅር አንድነት ማለት ጌታ ኢየሱስ ሁኖ እናገኘዋለን ።

በእውነትም ሰላማዊ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ የሚቀበል ምድራዊው የሰው ልጅ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ያዘዘውን ትእዛዝ በመጠበቅ መመሪያውን በመከተል በክርስቲያናዊ ሕይወት የሚኖር ቢሆን ኑሮ ፤ ይህች ምድራችን ጠብ ክርክር ሥጋት ፍርሃት ጦርነትና አልቂት የጠፉባት ወንድማማችነት እኩልነት ነጻነት ብልጽግና የሰፈኑባት የሰላም ደሴት ሁና ትኖር እንደነበር አያጠራጥርም ። ይሁን እንጂ ከላይ መግለጽ እንደ ጀመርነው የሰው ልጅ ግላዊ ፍላጎት የማይገታ በመሆኑና ይህንንም ግላዊ ፍላጎቱን ለማርካት በሚያደርገው ጥረት የጥንቱ መሣሪያው ዲያብሎስ ስለሚተባበረው እያንዳንዱ በየበኩሉ አንዱ ከሌላው የበለጠ ክብርና ዝና እንዲኖረው ፤ በሀገርም ደረጃ አንዱ ሀገር በሌላው ሀገር ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ምድራውያን ጥቅሞችን ፤ በሙሉ ለማግበስበስ ያለውን ምኞት ለማርካት በጦር በትራፊ ያካሔደው የነበረውን ጦርነት በማሳደግ አሁን እንዲያ ልፍ በመንካት ዓለምን በሙሉ በቅጽበት ሊደመስስ የሚችል መሣሪያ ከሚያመርትበት ደረጃ ደርሶ ይገኛል ። ይህ ዓይነቱ ሰይጣናዊ ውድድር በመቀጠል ላይ መሆኑን የዓለም ሕዝብ በሙሉ የሚያውቀው ነው ። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ አሁን የሚያቀላጥፈው ውድድር አጥፍቶ ለመጥፋት እንጂ በፃንም ተአምር ሌላውን አጥፍቶ እሱ ሊለማ ስለማይችል ይህንን የጥፋት መልእክቱን አስወግዶ ለእሱ ደኅንነት ሲል በቤተ ልሔም የተወለደለትን ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት ተቀብሎ «ላንተ ሊያደርጉብህ የማትፈልገውን በወንድምህ ላይ አታድርግ» የሚለውን የሰላም መልእክት በአንድነት ቢቀበል ሰላም በምድር የሚለው የመላእክት መልእክት ግልጽ ትርጉም እንደሚኖረው አንጠራጠርም ።

አሁንም የዓለም ክርስቲያን በዓለ ልደትን በማክበር ፤ ስጦታ በመለዋወጥ የሚያስታውሰን ክርስቲያንነቱን በተግባር መግለጥ ግዴታ አለበት ይኸውም ከሰማይ ሠራዊት ጋር በእግረ ሕሊና ቁሞ «ሰላም በምድር የሚለውን መዝሙር መዘመር ግዴታ አለበት ።

ክርስቲያኖች ክርስቲያንነታቸውን በተግባር ፤ የሚገልጹበት ጊዜ አሁን ነው ። እለዚያ ክርስቲያን ነኝ እያሉ ክርስቲያን ሊፈጽመው የማይገባውን ከክርስቶስ መመሪያ ውጭ የሆነውን ተንኮልን ምቀኝነት ዕብሪትንና በወንድም ላይ ተጽዕኖን በመፈጸም የሚደረገው እስጸያፊ ሥራ እግዚአብሔርን ለማታለል መሞከር ነውና ቂልነት ነው እንላለን ።

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የሁላችን የተሐድሶ ልደት መሆኑን አውቀን በመንፈስ እንታደስ ።

ሰላም ለመላዋ ዓለም ይዳረስ ፤

ከመምህር ሀብተ ማርያም ተድላ



www.ethiopianorthodox.org

# የምወደው ልጄ ይህ ነው

ይህ የምስክርነት ቃል የተነገረ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ቅድስተ ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ በተወለደ በ፴ ዓመቱ በማየ ዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ ነው ።

እንግዲህ ወላዲ እግዚአብሔር አብ ሲሆን ተወላዲ ግን የእግዚአብሔር የባህርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ እንመለከታለን ምሥጢሩም ከአብ ከባህርዩ የተገኘ ማለት ነው ። እግዚአብሔር አብም ከደመናው ያሰማው ድምጽ እንዲህ የሚል ነበር ዓለም ሊድንበት የመረጥሁትና የምወደው ልጄ ይህ ነው ሲል ተሰምቷል ። እሰቀለሁ እሞታለሁ ቢላችሁ ተቀበሉት እንጂ ይህ ሞት ባንተ ሊደረግ አይገባም አትበሉት እንዲሞትና በሞቱም ዓለምን እንዲያድን ቀደም ብሎ በነቢያት ትንቢት አናግሮአል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ ይህ ቃል የተነገረበት ፍሬ ነገርም ።

እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ አስቀድሞ አንድነት ሦስትነት በቱልሕ አልተገለጸም ነበርና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በማየ ዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ ከራሱ ላይ ሲያርፍበት እግዚአብሔር አብም በደመና ሁኖ ልጄ ይህ ነው ብሎ በመመስከሩ አንድነቱ ሦስትነቱ ተአውቋልና ። ከእግዚአብሔር አብም እንደተወለደ ራሱ መስክሯል ከአብ አካል ዘእም አካል ባህርይ ዘእም ባህርይ ተወልደ ወደዚህ ዓለም መጣሁ ብሏልና ። ዮሐ ፲፮ ፡ ቁ ፳፰ ።

ስለ ጥምቀትም በብሉይ ኪዳን እንደተነገረ ተገልጿል ። ውሃን እረጫባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ ተብሎ በትንቢተ ሕዝቅኤል ተነግሮአል (ሕዝ ፴፮ ቁ ፳፭) የጥምቀትን ጠቃሚነትና ከመንፈስ ቅዱስ የምንወለደውን ዳግም ልደት በሥራ ለማስረዳት ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃል ሳይሆን በሥራ ጥምቀትን መሥርቷልና ።

ስለዚህ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው ትምህርት ሁሉ የሕይወታችን መመሪያ ነው ። እንግዲህ ልናስተውለው የሚገባ አለ እርሱም ጥምቀት ተራ ሕግ ያለመሆኑን ሲያስረዳን እርሱ ተጠምቆ እኛም እንድንጠመቅ አዘዞናል ስንጠመቅም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደሆነ ተነግሮናል ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ መውረዱ እኛም ስንጠመቅ መንፈስ ቅዱስ እንደሚወርድብን ያስረዳል ። በመጠመቃችንም ከመንፈስ ቅዱስ እንደምንወለድ ሲገልጽ ከውሃና ከመንፈስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገባ በአፅንኦት ቃሉ አስተምሮናል ። ዮሐ ፫ ፡ ቁ ፡ ፭ ።

በሌላ በኩልም ጥምቀት ፍጹም ድህነተ ነፍስ እንደሠጠን ተገልጿል የአመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል ተብሎ ተነግሯልና ማር ፲፮ ፡ ቁ ፲፮ እንግዲህ ከእምነትና ከጥምቀት ክልል ውጭ የሆኑ ሰዎች ቢኖሩ አስተማሪ ካህን እያለ ተምሮ ለማመን አጥማቂ ቄስ እያለ ተጠምቆ ለመዳን ፈቃደኞች ሳይሆኑ ግን ያላመነ ያልተጠመቀ ይፈረድበታል ከሚለው አምላካዊ ፍርድ የሚያመልጡም አይደሉም ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትን የመሠረተ በጠቅላላ ለዓለሙ ሁሉ ድህነት እንጂ ለጥቂት ሰዎች አልነበረም የክርስቶስን ወገን ያልሆነ ሕዝብ የለምና ለስብከተ ወንጌልም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን በአስማራቸው ጊዜ ሂዳችሁ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ስታጠምቋቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው ብሎአልና ።

የእግዚአብሔር ልጆች የሚሆኑም በዮርዳኖስ ውሃ ብቻ ሳይሆን በሥጋው በደሙ ተቀድሰው ከመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን አግኝተው መንፈስ ፡ ደም ውሃ ማለት ማየ ገቦ የመሰከረላቸው በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ ዮሐንስ ፭ ፡ ቁ ፡ ፯

በሌላ በኩልም ክርስቶስ በማየ ዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ በአዳምና በሔዋን ጠላታቸው ዲያብሎስ ጽፎባቸው የነበረውን የዕዳቸውን ደብዳቤ እንዳጠፋላቸው ይተረካል እንግዲህ ሰዎች ሁሉ ሲጠመቁ ኃጢአታቸው በጥምቀት እንዲሠረይላቸውና እንዲታደሱም ያስረዳል ።

ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቲቶ በላከው መልእክቱ «እንደቸርነቱ መጠን ለሐዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ በማለት የገለጸው ቲቶ ፫ ፡ ቁ ፡ ፫ በውሃ ለመጠመቃችንም ምሳሌ አለው ይህም የክርስቶስ የሞቱ ምሳሌ ነው ። ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ብርሃን መለኮቱን ተዋሕዶ እንደ ተነሣ እኛም ብርሃን ለብሰን ፡ ብርሃን ተጎናጽፈን እንነሣለንና ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላሣ ዘመን መጠመቁም በብሉይ ኪዳን ሌዋውያን በሰላሣ ዘመን ሥራ የሚጀምሩበት ሥነ ሥርዓት ነበራቸው ቃል ቁ ፡ ፬ ፡ ፫ እርሱም በሠላሳ ዘመን ተጠምቆ ሥራውን በጾም ጀመሩ ከዚያም በኋላ ሐዋርያትን መረጠና ከአንዱ ሀገር ወደ ሌላው እየተዘዋወረ ወንጌልን አስተማረ ።



እንግዲህ የሰው ልጆች ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ እንደሚጠብቅባቸው ያስረዳል ። በሌላ በኩልም ጌታ በሰላሣ ዘመን ከተጠመቀ እኛም በአርባ ቀን እንድንጠመቅ ለምን ተደረገ የሚሉ ጠያቂዎች መኖራቸው ይታወሳል ። መልሱ ግን ቅርብ ነው ። ሠላሣ ዘመን ሣይሞላው ቢሞት ግን ከመንፈስ ቅዱስ ልጅነት ሳያገኝ እንዳይሞት በማለት ወንዶች በአርባ ቀን ሴቶች በ፹ ቀን እንዲጠመቁ ተደርጎአል ። ግን አርባ ቀን ሳይሞላው ሕጻኑ ለልት የሚያበቃ ሕማም ቢታመም ግን ከአርባ ቀን ጎድሎ ሴቶችም ከ፹ ቀን ጎድሎ እንዲጠመቁ ሥርዓት ተሠርቷል ።

ምበንያቱም ከወሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባ ዘንድ አይችልም ተብሎ አልና እንግዲህ ከላይ ከፍ ብሎ በእርሱ ላይ እንደ ተገለጠ እግዚአብሔር አብ የምወደውና ዓለም በእርሱ ሊድንበት የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው በማለት የባህርይ አባትነቱን ለእግዚአብሔር ወልድ ሲመሰክር በመጥምቁ ዮሐንስ ፊት ተገልጿል ።

በሁለተኛ ጊዜም በ፴ ሁለት ዓመተ ምህረት በረጅም ተራራ ላይ ጌታ ኢየሱስ ባህርየ መለኮቱን ለጴጥሮስና ለያዕቆብ ለዮሐንስ ም ከነቢያትም ለሙሴና ለኤልያስ በገለጠ ጊዜ ይህ ቃል እንደተነገረ ሦስቱ ወንጌላውያን የምስክርነት ቃላቸውን በጻፉት ቅዱስ ወንጌል ገልጠዋል ።

እንግዲህ ዓለም ሊድንበት እንደመረጠውና እንደወደደው ሲያስረዳ በአንድ የባህር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ መሰዋዕትነት ዓለምን አድኖበታል ለአባቱ ፈቃደኛ የሆነ ልጅ እጅግ በአባቱ ዘንድ የተወደደና የተመረጠ ይሆናል ። እንደዚሁም ሁሉ እሺ በእጄ ብሎ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ለሰላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በፈጸመው አምላካዊ ሥራ ለባሕርይ አባቱ የተወደደና የተመረጠ የባህርይ ልጅነቱን አስረድቶናል ። እኛም በጥምቀቱ ጊዜ የተገለጠውን የአንድነትና የሦስትነትን ምሥጢር አስተምሮን ለሃይማኖታችን ንንድን ምስክር እግዚአብሔር በረድኤት ከእኛ ጋር ይሁን ።

ከመምህር ኪዳን ማርያም አየለ



www.ethiopianorthodox.org